# የመምህሩ መምሪያ

## የመጽሐፍ ቅዱስ ጊዜ ደረጃ 1 እና 2

ስርዓተ ትምህርት ለ

ለ7 – ለ 12

**የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርታዊ አገልግሎቶች**
በእንግሊዝ የበጎ አድራጎት ምዝገባ (ቁጥር 1096157)

**የተልዕኮ መልእክት**
የአሁኑንና መጪውን ትውልድ በእግዚአብሔር ቃል ለመድረስ ለዓለም አቀፋዊ ግልጋሎት የሚውሉ ተከታታይ የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርቶችን ለእርስዎ በማዘጋጀት እርስዎም ሌሎችንም እንዲያገለግሉ ለማድረግ ነው።

**የራእይ መልእክት**
የዓለም ቋንቋዎችን በተለያዩ የመገናኛ አውታሮች በመጠቀም በእኛ ማዕከላዊ እሴቶች መሠረት የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርታዊ መረጃዎችን ከእኛ ጋር ለሚሠሩ ሁኔታዎችን ማመቻቸት ነው።

**ጠቅላላ መረጃ**
**የመጽሐፍ ቅዱስ የትምህርት አገልግሎት ምን እንደሚያከናውን:-**

መጽሐፍ ቅዱሳዊ የትምህርት አገልግሎት (ቢኢኤስ) በኢንግሊዚኛ የተዘጋጁ፡፡ የአዲስ ህይወትን እና የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርቶችን ሰብስቦ በማሣተም፣ በፖስታ ቤት በኩል የሚሠጡ ትምህርቶችንና ሌሎች ተመሣሣይ በእንግሊዝ እንዲሁም በሌሎች አገሮች የሚሠሩ ድርጅቶችን በቢኢኤስ በኩል በመንብኘት፣ በማስተሣሠር፣ በማስተዋወቅና በማሠልጠን ይረዳል። ከዚህ በተጨማሪም ቢኢኤስ በአሁኑ ወቅት በሌሎች አገሮች ውስጥ ትምህርቶችን በመተርጎም፣ በመንደፍ፣ በማሣተምና በማሠራጨት ሥራ ላይ ከተሠማሩ ቡድኖች ጋር አብሮ ይሠራል። ትምህርቶቹ በመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ወቅት ለሁሉም ተማሪዎች በነፃ የሚሠጡ ሲሆን ይህም ለመጀመሪያ ጊዜ በደቡብ አየርላንድ ከ50 ዓመታት በፊት ተጀመረ። የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት አገልግሎት አዘጋጆች በመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ወቅት በኢንግሊዚኛና በሌሎች ቋንቋዎች ለሚዘጋጁ ትምህርቶች ኃላፊነት አለባቸው። ብዙውን ጊዜ በመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ወቅት

የሚዘጋጁ ትምህርቶች የሚታተሙት በA4 ፎርማት (አቀራረብ) ሲሆን ይህም በሌሎች አከባቢዎች የሚገኙ ተማሪዎች በየአራት ሣምንቱ ፈተናው ወደ ሚታረምበት የመጽሐፍ ቅዱስ ማዕከል ለመላክ እንዲያመች ነው። በአሁኑ ጊዜም ለእያንዳንዱ ቤት የወንጌል ሥርጭት መነቃቂያዎች ምስጋና ይግባውና በቤል ፋስት ውስጥ ለስድስት ወራት የሚያገለግል ትምህርት በA5 ፎርማት (አቀራረብ) ስለሚታተም በተላይም የፖስታ አገልግሎት በማይገኝባቸው አብያተ ቤተ ክርስቲያናትና ትምህርት ቤቶች ጉዳዩን በጣም እንዲቀላጠፍ አድርጎታል። ቢኢኤስ በባህሪይው የሚለየው የሚዘጋጁት ትምህርቶች የቤት ወይም የቡድን ጥናትን ያማከሉና ተማሪዎቹም ሥርዓተ ትምህርቱን እስከ 20 ዓመታት ድረስ በቤተ ክርስቲያን/ትምህርት ቤት ያለማቋረጥ እንዲከታተሉ ስለሚያደረግ ነው። ለተወሠኑ የዕድሜ ደረጃ ቡድኖች የሚያገለግሉ አምስት የትምህርት ደረጃዎች ያሉ ሲሆን እነርሱም የቅድመ-ትምህርት ቤት፣ ከ5-7፣ ከ8-10፣ ከ11-13ና ከ14-16 ናቸው። ለእያንዳንዱ ቡድን የሶስት ዓመታት ሥርዓተ ትምህርት ይዘጋጃል። በተመሣሣይ የእድሜ ክልል ውስጥ ያሉ የቡድን አባላት የተለያዩ ችሎታዎች ሊኖራቸው ይችላል። የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት መረጃዎች ለልጆች የእግዚአብሔርን ቃል፣ የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪኮችንና በህይወታቸው የወንጌልን ጠቃሚነት ተግዳሮቶችን እንዲጋፈጡ እድል ይሠጣቸዋል።

በኢንግሊዚኛ ለትምህርት ተዘጋጅተው የታተሙ ቅጂዎች ከቢኢኤስ ድህረ ገጽ - www.besweb.com ወይም ከዓለም አቀፍ ጽህፈት ቤቱ ይገኛሉ። በድህረ ገጹ ላይ በሌሎች ቋንቋዎችም ይገኛሉ። ጽህፈት ቤቱ የቢኢኤስ ማዕከል ለማቋቋም የሚረዱ መረጃዎችን አለው።

## የቢኢኤስ መገኛ አድራሻዎች

**ዓለም አቀፋዊና የሠሜን አየርላንድ ጸሐፊ (ለትምህርት የተዘጋጁ ጽሁፎች በሙሉ)**
Mr S Balmer, 37a Belmore Street, Enniskillen, Northern Ireland. BT74 6AA
Phone: 0286 632 2462
Email: sam@besweb.com

**ድህረ ገጽ**: www.besweb.com
**ኢሜል**: info@besweb.com

## ለአስተማሪዎች የሚያገለግሉ መመሪያዎች በመጀመሪያ

የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርቶች ይዘጋጁ የነበሩት በፖስታ ትምህርት ቤት ማዕከል በኩል ቢሆንም ትምህርቶቹ በከፍተኛ ደረጃ ጥቅም ላይ የዋሉት የፖስታ ቤት ሥርዓት አስተማማኝ ባልሆነባቸው ወይም በማይገኝባቸው በአፍሪካ፤ በህንድና በሌሎችም ቦታዎች በሚገኙ አብያተ ክርስቲያናትና ትምህርት ቤቶች ነበር። የማስተማሪያ መመሪያዎች የተዘጋጁት የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት በሚካሄድበት ወቅት በጥቅም ላይ እንዲውሉ ነው። በዚህ ትንሽ መጽሐፍ ውስጥ እንዲያገለግል የተዘጋጀው የማስተማሪያ መመሪያ እድሜያቸው ከ11-16 ለሆኑ በደረጃ 3 እና 4 ለሚገኙ ተማሪዎች ነው። በእያንዳንዱ ሣምንት የሚሠጠው መመሪያ ተመሣሣይ የመጽሐፍ ቅዱስ ማጣቀሻዎችን ይጠቀማል። ስለሆነም የሚያዚያ ትምህርቶች የሚያተኩሩት በፋሲካ በዓል ላይ ሲሆን የታህሳሶቹ ደግሞ ትኩረታቸው በገና በዓል ላይ ነው።

አንዳንድ ቦታዎች በየሣምንቱ በA4 የሚዘጋጅ ትምህርት ሲኖራቸው ሌሎቹ ደግሞ ባለ A5 24 ትምህርቶችን የሚይዝ ትንሽ መጽሐፍ ይጠቀማሉ። ብዙውን ጊዜ አስተማሪው ወይም መሪው የየወሩን A4 ትምህርቶች ለተማሪዎቹ በቤተ ክርስቲያን ወይም ትምህርት ቤት ወይም ቤት ወርክ ሺቱን ሠርተው በሚቀጥለው ሣምንት እንዲያመጡት ያደርጋል። በወሩ መጨረሻ አስተማሪው ወይም መሪው ወርክ ሺቱ ላይ የተሠሩትን ትምህርቶች በመሠብሠብና በማረም በተሻለ ፍጥነት ተማሪዎቹ እንዲደርሳቸው ያደርጋል።

ትንንሽ መጽሐፍቱ በሥራ ላይ በሚውሉበት ወቅት በእያንዳንዱ ትምህርት መጨረሻ ተሠብስበው ይታረማሉ። በብዙ አጋጣሚዎች እንደዚህ ማድረግ እንደማይሣካ እንገነዘባለን። ስለዚህ አስተማሪው ወይም መሪው የሚታረሙትን ትምህርቶች በክፍል ውስጥ በማሠራጨትና መልሶችን በመስራት ተማሪዎቹ የጓደኞቻቸውን አርመው ውጤት እንዲሠጡ ያደረጋል። በመጽሐፉቶቹ የመጨረሻ ገፆች ላይ የተማሪዎቹ ወርሃዊ የትምህርት ውጤት የሚቀመጥበትና የተማሪው የመሻሻል ሁኔታ አስተያየት የሚፃፍበት ባዶ ቦታ አለ። ተማሪው በስድስት ወራት ውስጥ ያስመዘገበውን ውጤት የሚያሣይ የምስክር ወረቀትም በየመጨረሻው ገጽ ተያይዟል።

## ለአስተማሪዎች የሚያስፈልግ ዝግጅት

በዚህ የማስተማሪያ መጽሐፍ ዝግጅት ላይ መመሪያ ሠጪዎች በመሆን አስተማሪው የራሱን ሃሣብና ተነሣሽነት እንዲጠቀም ፈጽሞ ትዕዛዝ አንሠጥም። ከዚህ ቀጥሎ ያሉት በመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ጊዜ የምትጠቀምባቸው መመሪያዎች ናቸው።

- **ታሪኩን በሚገባ ተረዱ** - አስተማሪዎች በተቻለ መጠን የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪኮችንና በመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ወቅት ከሚሠጡ ትምህርቶች ጋር በሚገባ መለማመድ አለባቸው። በመሠረቱ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ትምህርት ከመሰጠቱ በፊት በአስተማሪው መጠናቀቅ አለበት። ለእያንዳንዱ ትምህርት የሚዘጋጁ መመሪያዎች እንደ ትምህርት መርጃ መሣሪያ ያገለግላሉ።
- **የምታስተምሩትን ትምህርት በሚገባ ተረዱ** - እያንዳንዱ የትምህርት እቅድ ከተጠናቀቀ በኋላ ፡፡ይህንን እንማራለን፡፡ ከሚሉ ትዕዛዛት ባሻገር ልጆች የአስተማሪውን ትምህርት ከተከታተሉና በመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ጊዜ ያገኙትን ትምህርት ሲያጠናቅቁ ሁለት የትምህርቱ ግቦች መሣካታቸውን ማስተዋል ትችላለህ። የመጀመሪያው ሃሣብ የታሪኩን እውቀት የሚያስገነዝብ ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ ልጆች ስለ ታሪኩ እንዲያስቡ፤ ተግባራዊ እንዲያደርጉና ምላሽ እንዲሠጡ ያበረታታል። እነዚህ ሃሣቦች ከትምህርቱ የተገኙ ትክክለኛዎቹ የዋናው ጽንሰ ሃሣብ/እውነታ በመሆናቸው አስተማሪዎች እነዚህን በመማር ማስተማሩ ግምገማ ወቅት መጠቀም ይችላሉ።
- **አስተዋውቁ** - በሁሉም ትምህርቶች ልጆች ካሉበት ሁኔታ ልምምድ እንጀምራለን። በታሪኩ መጀመሪያ ልጆች እንዲወያዩበት ለማስቻል የተለያዩ መንገዶችን እንደ መግቢያ እንጠቁማለን።

- **አስተምሩ** - በታሪኩ ውስጥ ቁልፍ ነጥቦችን ሠጥተናል። አስተማሪው በሚያስተምርበት ወቅት የእነዚህን ቁልፍ ነጥቦች ሃሣብ በሚገባ ተረድቶ እንጂ ሲያስተምር እንደ ማጣቀሻ ሣይጠቀም በሚያስደስትና በሚስብ መልኩ ማስተማር አለበት። አስተማሪው ልጆቹ ከታሪኩ ዋናውን ትምህርት እንዲረዱለትና ከተማሩት ታሪክ የሚሠጡትን ምላሽ መረዳት ይፈልጋል። ተገቢ በሆነበት ቦታ ሁሉ ጥቂት ማብራሪያዎችን ከሚነገረው ታሪክ ጋር እንዲቀናጅ ለማድረግ ሞክረናል። እነዚህ ሁል ጊዜ በተለየ የአፃፃፍ ስልት /ኢታሊክስ ይቀመጣሉ።
- **አስጠኑ** - ከእያንዳንዱ ታሪክ ጋር የተያያዘ መሪ ጥቅስ አለ። በጥቂት አጋጣሚዎች ሁለት መሪ ጥቅሶች የተሠጡ ሲሆን ይህም ለልጆች ትምህርት በቀላሉ እንዲያገለግል ነው። ልጆች እነዚህን መሪ ጥቅሶች እንደሚማሯቸው ተስፋ ስለምናደርግ ሁል ጊዜ እያስታወሱ በመጽሐፍ ቅዱስ መሪ ጥቅሶች ላይ የተመሠረተ እውቀት እንዲገነቡ ማድረግ ነው።
- **አጠናቁ** - በትምህርት ቤት ውስጥ የልጆችን ችሎታ በሚያጠናቅቁት ዎርክ ሺትና የሚሠጡትን የአስተማሪው መርጃ መረዳት ይቻላል። ለጥቂቶች የሚያስፈልገው ነገር አስተማሪው የመማሪያ መጽሐፉን ታሪክ ተማሪዎቹ እንዲለምዱት ለማድረግ ማንበብ ነው። ሌሎች ተማሪዎች ደግሞ የመማሪያ መጽሐፉን እራሣቸውን ችለው እንዲያነቡ ማድረግ ነው። ከሁለቱ አንደኛውን መንገድ በመጠቀም የተማሪዎችን ትኩረት ወደ አንድ ጥያቄ ወደ ሚመልስ ርእስ ማድረስ ነው። ከትምህርት ቤት ውጪ መጽሐፍ ቅዱስን የምትጠቀም ከሆነይህ ተማሪዎችን ሊረዳ በሚችል መልኩ መቅረብ አለበት እንጂ የሚያሰለች ሥራ ወይም ፈተና መሆን የለበትም። ሥራው በሚሠራበት ወቅት አስደሣች፤ የሚያበረታታና ወደ አምልኮ የሚመራ መሆን አለበት። ይህ ጠቃሚና የሚያስደስት ሥራ ተግባራዊ ሲሆን ያበረታታል።

- **እዲታወስ** - በሚቻልበት ቦታ ሁሉ መልመጃዎች ወይም የመማሩን ሂደት የሚደግፉና ታሪክን እንደገና የምንከልስበት ሁኔታ መጠቀም እንደሚያስፈልግ እንመክራለን።

- **አሳዩ** - በአንዳንድ ጥቂት አጋጣሚዎች የሚታዩ መርጃ መሣሪያዎችን ለማግኘት በጣም አስቸጋሪ ቢሆንም በተገኘው አጋጣሚ ሁሉ ታሪክን ለመረዳት በሥዕሎች ወይም በነገሮች ላይ ትኩረት ማድረግ ይጠቅማል። የሚታዩ መርጃ መሣሪያዎች ታሪክን ለመናገር ጠቃሚዎች ናቸው። ለእያንዳንዱ ትምህርት ተገቢ የሆኑትን ምሥሎች ከሚከተለው ድህረ ገጽ www.freebibleimages.org ማውረድ ይቻላል። ሌላው የሚታይ መረጃ Eikon Bible Art [info@eikonbibleart.com] ሲሆን ይህንን ማስረጃ ግን ማግኘት የሚቻለው በግዢ ነው። ፎቶ ኮፒ በሚገኝበት ቦታ ጥቂት በመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ጊዜ የሚያገለግሉ ሥዕሎችን ማድመቅ፤ ቀለም መቀባባትና ለትምህርት መጠቀም ይቻላል።

**ቁልፍ ጥቅሶችን ማስተማር**

ጥቅሱ በልሙጥ ወረቀት ወይም በሠሌዳ ላይ የሚፃፍ ሲሆን ልጆቹ ጥቅሶቹ እስኪያዙና ቃላቶቹ እስኪያልቁ ሂደቱን መቀጠል ሲጠበቅባቸው ቃላቶቹ ካለቁም በኋላ ጥቅሶቹን ይደጋግማሉ።

መሪ ጥቅሱን ለማስተዋወቅ የሚከተለውን አካሄድ ተጠቀም።

1. ሁለት የፊደል ጨዋታ ተወዳዳሪ ቡድኖች ያስፈልጋሉ- የፊደላት ብዛት- የዋናው መሪ ጥቅስ ክፍት ቦታ ያለ ምንም ፊደላት ይቀመጥ- ልጆቹ የሚፈልጉትን ፊደላት እየመረጡ አንድ ልጅ ጥቅሱን እስኪያነበየው ድረስ ጨዋታው ይቀጥላል።
2. መጽሐፍ ቅዱስ በሚገኝበት ወቅት የመጽሐፍ ጥቅስ ጨዋታ ይካሄዳል። ልጆች ጥቅሱን ለማግኘት ይሽቀዳደማሉ፤ ጥቅሱንም መጀመሪያ ያገኘው ድምፁን ከፍ አድርጎ ያነባል።

**መርሀ ግብር**

ቅደም ተከተል:- በማስተማሪያ መመሪያዎች ውስጥ ያስቀመጥነው ቅደም ተከተል ለዚህ ትምህርት ቢያገለግልም አስተማሪው ቅደም ተከተሉን ከጊዜ ወደ ጊዜ ሊቀያይር ይችላል።

- መግቢያና ታሪክን ለመናገር - በግምት 15 ደቂቃዎች
- መሪ ጥቅሱን ለማስተማር - 5-10 ደቂቃዎች
- ወርክ ሺቱን ለማጠናቀቅ - 20 ደቂቃዎች
    - ለሙከራና ሌሎች እንቅስቃሴዎች - 5-10 ደቂቃዎች ይበቃሉ።

ጠቃሚው አባባል ምን እንደሚል አስታውሱ:

‘ብትነግረኝ ልረሣው እችላለሁ፤  
ብታሣየኝ አስታውሰዋለሁ፤  
ብታሣትፈኝ እረዳዋለሁ።”

# የመጽሐፍ ቅዱስ ጊዜ  ሥርዓተ ትምህርት

| | ደረጃ 0 (ቅድመ-ት/ት)<br>ደረጃ 1 (እድሜ 5-7)<br>ደረጃ 2 (እድሜ 8-10) | ደረጃ 3 (እድሜ 11-13) | ደረጃ 4 (እድሜ 14+) |
|---|---|---|---|
| የጀማሪዎች ስርዓተ ት/ት | 1. የማሟሟቂያ ትምህርት-መግቢያ<br>2. ምዕራፍ 1 - የሉቃስ ወንጌል<br>3. ምዕራፍ 2 - የሉቃስ ወንጌል<br>4. ምዕራፍ 3 - የሉቃስ ወንጌል | 1. የማሟሟቂያ ትምህርት- መግቢያ<br>2. ምዕራፍ 1 - የሉቃስ ወንጌል<br>3. ምዕራፍ 2 - የሉቃስ ወንጌል<br>4. ምዕራፍ 3 - የሉቃስ ወንጌል | 1. የማሟሟቂያ ትምህርት- መግቢያ<br>2. ምዕራፍ 1 - የሉቃስ ወንጌል<br>3. ምዕራፍ 2 - የሉቃስ ወንጌል<br>4. ምዕራፍ 3 - የሉቃስ ወንጌል |
| ስርዓተ ት/ት ሀ | 1. ፍጥረት<br>2. ኖህ<br>3. ጴጥሮስ<br>4. የጴጥሮስ - መስቀል<br>5. አብርሃም<br>6. አብርሃም<br>7. ጴጥሮስ<br>8. ጴጥሮስ<br>9. ያዕቆብ<br>10. የጥንት ክርስቲያኖች<br>11. ጳውሎስ<br>12. የገና ታሪክ | 1. ፍጥረት<br>2. ኖህ<br>3. ጴጥሮስ<br>4. የጴጥሮስ - መስቀል<br>5. አብርሃም<br>6. አብርሃም<br>7. ጴጥሮስ<br>8. ጴጥሮስ<br>9. ያዕቆብ<br>10. የጥንት ክርስቲያኖች<br>11. ጳውሎስ<br>12. የገና ታሪክ | 1. ፍጥረት<br>2. ኖህ<br>3. ጴጥሮስ<br>4. የጴጥሮስ - መስቀል<br>5. አብርሃም<br>6. አብርሃም<br>7. ጴጥሮስ<br>8. ጴጥሮስ<br>9. ያዕቆብ<br>10. የጥንት ክርስቲያኖች<br>11. ጳውሎስ<br>12. የገና ታሪክ |
| ስርዓተ ት/ት ለ | 1. የመጀመሪያው የክርስቶስ ኑሮ<br>2. ተዓምራት<br>3. ቢታኒያ<br>4. መስቀሉ<br>5. ምሣዎች<br>6. ዮሴፍ<br>7. ዮሴፍ<br>8. ኢየሱስ ያገኛቸው ሰዎች<br>9. ሙሴ<br>10. ሙሴ<br>11. ሙሴ<br>12. የገና ታሪክ | 1. ምሣሌዎች<br>2. ተዓምራት<br>3. ቢታኒያ<br>4. መስቀሉ<br>5. የጥንት ክርስቲያኖች<br>6. ዮሴፍ<br>7. ዮሴፍ<br>8. የወንጌል ጸሐፊዎች<br>9. ሙሴ<br>10. ሙሴ<br>11. ሙሴ<br>12. የገና ታሪክ | 1. ምሣሌዎች<br>2. ተዓምራት<br>3. ቢታኒያ<br>4. መስቀሉ<br>5. የጥንት ክርስቲያኖች<br>6. ዮሴፍ<br>7. ዮሴፍ<br>8. የወንጌል ጸሐፊዎች<br>9. ሙሴ<br>10. ሙሴ<br>11. ሙሴ<br>12. የገና ታሪክ |
| ስርዓተ ት/ት ሐ | 1. ዳንኤል<br>2. ብዙ ተዓምራት<br>3. ብዙ ተዓምራት<br>4. የክርስቶስ ሞት<br>5. ሩትና ሣሙኤል<br>6. ዳዊት<br>7. ዳዊት<br>8. እያሱ<br>9. ኤልያስ<br>10. ኤልሣ<br>11. ዮናታን<br>12. የገና ታሪክ | 1. ዳንኤል<br>2. ብዙ ተዓምራት<br>3. ብዙ ተዓምራት<br>4. የክርስቶስ ሞት<br>5. ሩትና ሣሙኤል<br>6. ዳዊት<br>7. ዳዊት<br>8. እያሱ<br>9. ኤልያስ<br>10. ኤልሣ<br>11. ዮናታን<br>12. የገና ታሪክ | 1. ዳንኤል<br>2. ብዙ ተዓምራት<br>3. ብዙ ተዓምራት<br>4. የክርስቶስ ሞት<br>5. ሩትና ሣሙኤል<br>6. ዳዊት<br>7. ዳዊት<br>8. እያሱ<br>9. ኤልያስ<br>10. ኤልሣ<br>11. ዮናታን<br>12. የገና ታሪክ |

<u>ለ7 ታሪክ 1</u>

**የዮሴፍ ወንድሞች ደረሱ – ይህ ታሪክ መጥፎ ነገር የማድረግን ውጤት የሚያሳይ ነው፡፡**

| | |
|---|---|
| | **እየተማርን ያለነው:**<br>• የሴፍ ስለ ወንድሞቹ ያለመው ህልም እውን መሆኑን፡፡<br>• የምናደርጋቸው መጥፎ ነገሮች በቶሎ ወይም ዘግይተው ይደርሱብናል፡፡<br><br>**ቁልፍ ጥቅስ: ገላቲያ 6: 7**<br>**የመጽሐፍ ቅዱስ የንባብ ክፍል: ዘፍጥረት 42:1-26** |
| እስተዋውቁ | እስከዚህ ድረስ ያለውን የዮሴፍን ታሪክ ልጆቹ ጥንድ ጥንድ ሆነው እንዲወያዩባቸው አድርጉ፡፡እስካሁን ድረስ የተከሰቱትን መጥፎ እና መልካም ነገሮች ለመለየት ሞክሩ፡፡ ወንድሞቹ ምንም ቢያደርጉትም እንኳን ለዮሴፍ ግን ነገሮች ለመልካም እንደሆኑለት በመናገር አጠቃሉ፡፡ ወንድሞቹ ግን በከነአን ምድር እንዴት እየሆኑ ነው? ልጆቹን ***በዘኍልቁ 32: 23*** ላይ ያለውን ቁልፍ ጥቅስ አስታውሷቸው፡፡ ***'ኃጢአታችሁም እንዲያገኛችሁ እወቁ፡፡'*** |
| አስተምሩ | • በከነአን ምድር ሰዎች እየተራቡ ነበር፡፡ ሰዎች የሚበሉት ምግብ አልነበራቸውም፡፡ ያዕቆብ በግብፅ ብዙ የተከማቸ ምግብ መኖሩን ሰምቷል፡፡ የዮሴፍ ወንድሞች ለቤተሰቡ የሚሆን ምግብ ለመግዛት ወደ ግብፅ እንዲወርዱ ነገራቸው፡፡ ከዮሴፍ ታናሽ ወንድም ከቢኒያም በስተቀር ሁሉም ወንድሞቹ ሄዱ፡፡ ***(ዘፍጥረት 42: 1- 5)***<br><br>• በግብጽ ውስጥ ዮሴፍ ምግቡን የመሸጥ ሀላፊነት ነበረው፡፡ ወንድሞቹ በደረሱ ጊዜ ሁሉም መጡና ለግብፅ ገዢ ለዮሴፍ ሰገዱ! ***(ዘፍጥረት 42: 6-7)***<br><br>• *የሴፍን ከመሸጣቸው በፊት ስለ ወንድሞቹ ያለመውን ህልም ለልጆቹ አስታውሷቸው፡፡ አሁን ህልሞቹ እየተፈጸሙ ነው፡፡*<br><br>• የሴፍ ወንድሞቹን እንደማያውቃቸው ሆነ እነርሱም አላወቁትም ነበር፡፡ እንደ እንግዳ አያቸውና 'እናንተ ሰላዮች ናችሁ! ምድሪቱን ለመሰለል መታችኋል!' አላቸው፤ ወንድሞቹም ይህ እውነት አለመሆኑን ነገሩት፡፡ ታማኝ ሰዎች እንደሆኑና ሁሉም የአንድ አባት ልጆች እንደሆኑ ለዮሴፍ ነገሩት፡፡ 'አሁን የሌለ' ግን ወንድም እንደነበራቸው እና ቤታቸው ታናሽ ወንድም እንዳላቸው ለዮሴም ነገሩት፡፡ ዮሴፍም እውነት እየተናገሩ መሆን አለመሆናቸውን ለመፈተን ወደ ከነአን ተመልሰው ታናሽ ወንድማቸውን ከእነርሱ ጋር ይዘው እንዲመለሱ ጠየቃቸው፡፡ ግዴታ ተመልሰው እንዲመጡ ለማድረግ አንዱን ወንድማቸውን ስምኦንን እስር ቤት አስገባው፡፡ ***(ዘፍጥረት 42:8- 20)***<br><br>• በወንድሞቹ መካከል ምን እንደተፈጠረ ተወያዩ፡፡ ከእነዚህ ሁሉ አመታት በፊት ዮሴፍ ላይ መጥፎ ነገር እንዳደረጉ ያውቁ ነበር፡፡ ወንጀለኛ እንደነበሩና ኃጢአታቸውም ይዟቸው እንደነበር አስረዱ፡፡<br><br>• የሴፍን ባደረጉት ነገር እግዚአብሔር እየቀጣቸው እንደነበር እርግጠኛ ነበሩ፡፡ ዮሴፍ የሚያወሩትን ነገር ሰማቸው፡፡ዞር ብሎም አለቀሰ፡፡ ***(ዘፍጥረት 42: 21-24)***<br><br>• ዮሴፍ የወንድሞቹን ከረጢት እህል እንዲሞሉ ሰራተኞቹን አዘዘ፡፡ ገንዘባቸው ከረጢታቸው ውስጥ እንዲመለስ አደረገና ለጉዞ የሚሆን ምግብ ሰጣቸው፡፡ ወንድሞቹ አህዮቻቸው ላይ ጫኑና ወደ አባታቸው ለመመለስ ወጡ፡፡ ***(ዘፍጥረት 42: 25-26)***<br><br>**የመጽሐፍ ቅዱስ ጊዜ ትምህርቱን አጠናቁ፡፡**<br>**አሳዩ:** FBI ([www.freebibleimages.org](http://www.freebibleimages.org)) የዮሴፍ ወንድሞች ግብፅን ጎበኙ፡፡ |
| አስጠኑ | ቁልፍ ጥቅሱን አስፈላጊ በሆነበት ቦታ ላይ አስተምሩና አስረዱ፡፡ ***ገላቲያ 6: 7*** ኃጢአት ሁልጊዜ ችግር ውስጥ እንደሚከተን ልጆቹን አስታውሱ፡፡ ዘር እንደመዝራትና አንድ ቀን የዘራነውን ያንኑ እንደማጨድ እንደሆነ መጽሐፍ ቅዱስ ይናገራል፡፡ |
| እዲታወስ | ታሪኩን ለመከለስ እንዲረዳ ልጆቹን ቀጥሎ ያሉትን ጥያቄዎች ጠይቋቸው፡፡<br>• ወንድሞቹ ለምን ወደ ግብፅ መምጣት አስፈለጋቸው?<br>• ግብፅ ውስጥ እህሉን ማን ነበር የሚሸጠው?<br>• የዮሴፍ ወንድሞች አወቀውት ነበር?<br>• ዮሴፍ ወንድሞቹን ምንድን ናችሁ ብሎ ነበር የከሰሳቸው?<br>• ዮሴፍ ማንን ነበር ወደ ግብፅ እንዲያመጡ የፈለገው?<br>• የትኛው ወንድማቸው ነበር እስር ቤት የገባው?<br>• ወንድሞቹ ይሄ ሁሉ ነገር በራሳቸው ላይ ለምን ደረሰ ብለው አሰቡ? |

## <u>ለ7 ታሪክ 2</u>

**ቢኒያም እና መጥፎ ዜና - ይህ ታሪክ ኃጢአታችን እንዴት እንደሚታወቅብን የሚያሳይ ነው፡፡**

**እየተማርን ያለነው፡**

- ወንድሞቹ እንዴትም ቢያደርጉት እንኳን ዮሴፍ አሁንም ይወዳቸው ነበር፡፡
- እግዚአብሔር እያንዳንዳችንን ይወደናል እናም ለሰራናቸው ስህተቶች ይቅር ሊለን ይፈልጋል፡፡

**ቁልፍ ጥቅስ፡ *ኤፌሶን 4፡ 32***

**የመጽሐፍ ቅዱስ የንባብ ክፍል፡ *ዘፍጥረት 42፡ 26 – 44፡ 13***

### አስተዋውቁ

ልጆቹ ወንድሞቹ ከከነአን ወደ ግብፅ ሲመለሱ ከእነሱ እንደ አንዱ እንደሆኑ እንዲያስቡ አድርጉ፡፡ አሁን ቤተሰብዎ ለመመገብ የሚያስችል በቂ ምግብ አለዎት! ምን እየተሰማችሁ ነው? አሁን፣ ከረጢታችሁን ስትከፍቱ እህሉን ብቻ ሳይሆን ለእህሉ የከፈላችሁትንም ገንዘብ ስታገኙ አስቡት! ማን ነው እዚህ ያስቀመጠው? ወጥመድ ነበር? በግብፅ ያለው መሪ ሰርቀኸዋል ብሎ ያስብ ይሆን? ለተጨማሪ ምግብ እንዴት ወደ ግብፅ ልትመለስ ትችላለክ?

እንደ አማራጭ ተጨማሪ ቁሳቁሶችን ሰብስቡ (ከረጢት፣ ምግብና ብር) እና ለልጆቹ በተግባር አሳዩ፡፡

### አስተምሩ

- ወንድሞቹ አህዮቻቸው ላይ ጭነው ወደ ቤታቸው ተጓዙ፡፡ በመንገድ ላይ ሳሉ ለእህል የከፈሉት ገንዘብ ወደ ከረጢታቸው እንደተመለሰ ከወንድሞቹ አንዱ አየ፡፡ በጣም ፈርተው ነበር! ***(ዘፍጥረት 42፡ 26-28)***
- *የሴፍ ገንዘቡን ወደ ከረጢታቸው ለምን እንደመለሰው ልጆቹን ጠይቋቸው፡፡ ወንድሞቹ ይህ የተፈጠረው በዮሴፍ ላይ ባደረጉት ኃጢአት ምክንያት መሆኑን እንዳስተዋሉ ለልጆቹ አስታውሷቸው፡፡*
- ቤት ሲደርሱ ለአባታቸው ምን እንደተፈጠረ ነገሩት፡፡ የግብፅ መሪ ሰላዮች ናችሁ ብሎ እንደከሰሳቸው ነገሩት፡፡ ቢኒያምን ወደ እርሱ እንዲያመጡት ፈልጎ ነበር፡፡ ያዕቆብ ይሄን ሲሰማ እና ገንዘባቸው አሁንም ከረጢቱ ውስጥ እንዳለ ሲመለከት ፈራ፡፡ ***(ዘፍጥረት 42፡ 29-38)*** *ያዕቆብ ቢኒያም ወደ ግብፅ እንዲሄድ ይፈቅዳል ብላችሁ ታስባላችሁ?*
- ጊዜው ሲያልፍ ረሀቡም እየባሰ መጣ፡፡ የያዕቆብ ቤተሰብ ድጋሚ ተራበ፡፡ ወደ ግብፅ ሄደው ተጨማሪ እህል እንዲገዙ ወንድማማቾቹን ጠየቃቸው፡፡ ቢኒያምን ከእነርሱ ጋር ካልሆነ በስተቀር መሄድ እንደማይችሉ ይሁዳ ነገረው፡፡ የቢኒያምን ደህንነት ለመጠበቅ ሀላፊነቱን እንደሚወስድ ለአባቱ ነገረው፡፡ ያዕቆብ ምንም ነገር ማድረግ አልቻለም፡፡ የሚበሉት ምግብ ያስፈልጋቸው ነበር፡፡ ቢኒያም ወደ ግብፅ እንዲሄድ ተስማማ፡፡ ወንድሞቹ የገንዘቡን እጥፍ እና ለመሪውም ስጦታ እንዲወስዱ ነገራቸው፡፡ ***(ዘፍጥረት 43፡ 1-14)*** *ወንድሞቹ የግብፅን መሪ ለመጋፈጥ ሲሄዱ ምን የተሰማቸው ይመስላችኋል?*
- ወንድሞቹ ግብፅ ደረሱና በዮሴፍ ፊት ቆሙ፡፡ ዮሴፍም ቢኒያም ከእነሱ ጋር እንደሆነ ሲያይ፣ ቤቱ ውስጥ ለትልቅ ድግስ እንዲያዘጋጁላቸው ሰራተኞቹን አዘዛቸው፡፡ ስምኦንን ከእስር ቤት አስወጣው፡፡ ዮሴፍ ወደ ድግሱ ሲመጣ ወንድሞቹ በድጋሚ ሰገዱለት፡፡ *ለልጆቹ የዮሴፍን ህልም አስታውሷቸው፡፡* አባታቸው እንዴት እንደነበር ጠየቃቸውና ቢኒያምን አዋራው፡፡ ዮሴፍ ከማዘኑ የተነሳ ክፍሉን ለቆ ወጣ፡፡ *ከደረሰበት ነገር ሁሉ በኋላም ግን ወንድሞቹን ይወዳቸው ነበር፡፡ በተላይ ደግሞ ታናሽ ወንድሙ የነበረውን ቢኒያምን፡፡* ዮሴፍ ሲመለስ ምግቡ ቀርቦ ነበር እና አንድ ላይ ምግብ በሉ፡፡ ***(ዘፍጥረት 43፡ 15 -34)*** *የተሳሳተ ነገር በምናደርግት ጊዜ እንኳን እግዚአብሔር እንደሚወደን አስረዱ፡፡ ለኃጢአታችን ይቅርታ ከጠየቅን ይቅር ይለናል፡፡*
- በነገውም ወንድሞቹ እህል የሞላውን ከረጢት ይዘው ወደ ከነአን ጉዞ ጀመሩ፡፡ በዚህ ጊዜ ዮሴፍ ልዩ የሆነውን የብር ዋንጫውን ቢኒያም ከረጢት ውስጥ እንዲከተት አድርጎ ነበር፡፡ ዮሴፍ ዋንጫውን እንዲፈልጉ ከወንድሞቹ ኋላ ሰራተኞቹን ላከ፡፡ ዋንጫው የቢኒያም ከረጢት ውስጥ ተገኘ! በድጋሚ ወደ ግብፅ መመለስ ነበረባቸው!

  ***(ዘፍጥረት 44፡1-13)***

**የመጽሐፍ ቅዱስ ጊዜ ትምህርቱን አጠናቁ፡፡**

**አሳዩ፡** FBI የዮሴፍ ወንድሞች ከቢኒያም ጋር ወደ ግብፅ ተመለሱ፡፡

### አስጠኑ

ቁልፍ ጥቅሱን አስፈላጊ በሆነበት ቦታ ላይ አስተምሩና አስረዱ፡፡ ***ኤፌሶን 4፡ 32*** *'ይቅርታ' የሚለውን ቃል አብራሩ፡፡ እግዚአብሔር እንደሚወደን እና ለሰራነው ስህተት ይቅርታ ስንጠይቅ ሁልጊዜ ይቅር ለማለት ዝግጁ እንደሆነ ለልጆቹ አስረዱ፡፡*

### እዲታወስ

ታሪኩን ለመከለስ እንዲረዳ ልጆቹን ቀጥሎ ያሉትን ጥያቄዎች ጠይቋቸው፡፡.

- ወንድሞቹ ከረጢታቸው ውስጥ ምን ነበር ያገኙት?
- ያዕቆብ ቢኒያም ወደ ግብፅ እንዲሄድ ፈልጎ ነበር?
- ቢኒያምን ለመጠበቅ የተስማማው ማን ነበር?
- ቢኒያምን ሲያይ ዮሴፍ ምን ነበር የተሰማው?
- ዮሴፍ ወንድሞቹን አሁንም ይወዳቸው ነበር?
- የማን ከረጢት ውስጥ ነበር ዋንጫው የተገኘው?
- ይቅርታ ማድረግ ምን ማለት ነው?
- ከእግዚአብሔር ይቅርታ ያስፈልገናል? ለምን?

## <u>ለ7 ታሪክ 3</u>

**ይቅርታ እና መልካም ዜና - ይህ ታሪክ እርስ በእርሳችን እንዴት ይቅር መባባል እንዳለብን የሚያሳይ ነው፡፡**

**እየተማርን ያለነው፡**

- የሴፍ ወንድሞቹ ላደረጉበት ነገር ይቅር አላቸው፡፡
- እግዚአብሔር እያንዳንዳችንን ይወደናል እና ለሰራነው ስህተት ይቅር ሊለን ይፈልጋል፡፡

**ቁልፍ ጥቅስ፡** ***ዘፍጥረት 45፡ 8***
**የመጽሐፍ ቅዱስ የንባብ ክፍል፡** ***ዘፍጥረት 44፡ 14 – 45፡ 28***

### አስተዋውቁ

እስከዚህ ድረስ ያለውን የወንድሞቹን ወደ ግብፅ ያደረጉትን ጉብኝት ለልጆቹ አስታውሱ፡፡ የዮሴፍ ንብረት የሆነው የብሩ ዋንጫ በቢኒያም ከረጢት ውስጥ ተገኝቷል፡፡ ወንድሞቹ በከበደ ልብ ወደ ግብፅ ተመለሱ፡፡ መሪው ምን ያደርግ ይሆን? ቢኒያም ይገደል ይሆን ወይስ እንደ ሰራተኛ ሆኖ እንዲቆይ ይገደድ ይሆን? ያለ ቢኒያም ወደ ከነአን ቢመለሱ አባታቸው ምን ይሆን ይሆን?

### አስተምሩ

- ወንድሞቹ ተመልሰው ወደ ዮሴፍ ቤት ደረሱ፡፡ የብር ዋንጫውን በመውሰዳቸው በጣም የተናደደ ለመምሰል ሞከረ፡፡ ይሁዳ ተናገረ፡፡ ይህ አስከፊ ሁኔታ የተፈጠረው ጥፋተኛ ሰዎች በመሆናቸው እንደሆነ ያውቅ ነበር፡፡ *'ጥፋተኛ' የሚለውን ቃል አብራሩ፡፡* ወንድሞቹ የዮሴፍ አገልጋዮች ለመሆን ሀሳብ አቀረቡ፡፡ ነገር ግን ዮሴፍ ከረጢቱ ውስጥ ዋንጫው የተገኘበት ሰው ብቻ ሰራተኛው ሆኖ እንደሚቀር ተናገረ፡፡ ቢኒያም መቅረት ነበረበት**!** ***(ዘፍጥረት 44፡ 14-17)***

- ይሁዳ በድጋሚ ዮሴፍን አናገረው፡፡ ቢኒያም ወደ ቤት ካልመጣ አባቱ ከሀዘን የተነሳ እንደሚሞት ለዮሴፍ ነገረው፡፡ ይሁዳ በቢኒያም ምትክ ሆኖ ለመቆየት ፈቃደኛ መሆኑን ገለጸ፡፡ ***(ዘፍጥረት 44፡ 18-34)*** *ወንድሞቹ እንዴት ልባቸው ሊለወጥ እንደቻለ አስረዱ፡፡ የሴፍን ለባርነት የመሸጥ ሀሳብ የነበረው ወንድም አሁን እርሱ ራሱ ባሪያ ለመሆን ፈቃደኛ ሆነ! ዮሴፍ ወንድሞቹ እርስ በእርሳቸው እንደሚተሳሰቡ እና ለአባታቸውም እንደሚያስቡ ተመለከተ፡፡*

- ዮሴፍ ለወንድሞቹ በትክክል ማን እንደሆነ ለመናገር ጊዜው እንደደረሰ ያውቅ ነበር፡፡ ከወንድሞቹ በስተቀር ሁሉም ሰው ክፍሉን ለቆ እንዲወጣ ጠየቀና፣ 'እኔ ዮሴፍ ነኝ፡፡' አለ፡፡ ወንድሞቹ መጀመሪያ ላይ ተጨንቀው ነበር፡፡ ዮሴፍ መበቀል ይፈልግ ይሆን? ሆኖም፣ ዮሴፍ ከመጀመሪያ ጀምሮ ይህ ሁሉ የእግዚአብሔር እቅድ አካል እንደሆነ አረጋገጠላቸው፡፡ በረሀብ ወቅት ህይወታቸውን ለማዳን በዚያ እንዲሆን እግዚአብሔር ከእነርሱ ፊት ወደ ግብፅ ልኮታል፡፡
***(ዘፍጥረት 45፡ 1-8)***
*ዮሴፍ ወንድሞቹን ይቅር የማለቱን እውነታ አስረዱ፡፡ ለተሳሳትናቸው ነገሮች ከልባችን ስንጸጸት እግዚአብሔር ይቅር ይለናል፡፡ በታሪኩ ውስጥ ልክ እንደ ይሁዳ ሁሉ እኛም ጥፋተኞች መሆናችንን መረዳትና በህይወታችን ውስጥ ላሉ የተሳሳቱ ነገሮች ሀላፊነትን ለመውሰድ ዝግጁ መሆን አለብን፡፡*

- ገና ተጨማሪ አምስት የረሀብ አመታት እንዳሉ ዮሴፍ ያውቅ ነበር፡፡ የቤተሰቦቹን ደህንነት ለመጠበቅ ፈልጓል፡፡ ቤት ሄደው ለአባታቸው ምን እንደተፈጠረ እንዲነግሩት አዘዛቸው፡፡ ከዚያ ንብረታቸውን ሁሉ ጠቅልለው በግብፅ ለመኖር ይመጣሉ፡፡ ***(ዘፍጥረት 45፡ 9-28)***

**የመጽሐፍ ቅዱስ ጊዜ ትምህርቱን አጠናቁ፡፡**
**አሳዩ፡** FBI ዮሴፍ ከቤተሰቡ ጋር ዳግም ተቀላቀለ፡፡

### አስጠኑ

ቁልፍ ጥቅሱን አስፈላጊ በሆነበት ቦታ ላይ አስተምሩና አስረዱ፡፡ ***ዘፍጥረት 45፡ 8*** (የጥቅሱን የመጀመሪያ ክፍል ብቻ ተጠቀሙ) በዮሴፍ ህይወት የተከሰቱት ነገሮች ሁሉ በረሀብ ወቅት እግዚአብሔር የያዕቆብን ቤተሰብ ለማዳን ያደረገው የእግዚአብሔር እቅድ አካል መሆኑን ለልጆቹ አስታውሷቸው፡፡

### እዲታወስ

ታሪኩን ለመከለስ እንዲረዳ ልጆቹን ቀጥሎ ያሉትን ጥያቄዎች ጠይቋቸው፡፡.

- የቢኒያም ከረጢት ውስጥ ምን ነበር የተገኘው?
- ዮሴፍ እንደ ሰራተኛ ሆኖ እንዲቀር የፈለገው ማንን ነበር?
- በቢኒያም ቦታ ሆኖ ለመቅረት የፈቀደው ማን ነበር?
- ቢኒያም ወደ ቤት ባይመለስ ያዕቆብ ምን ይሆን ነበር?
- ወንድሞቹ ልባቸው እንደተለወጠ ዮሴፍ እንዴት አወቀ?
- ዮሴፍ ወንድሞቹን ይቅር ብሎ ነበር?
- ኃጢአታችን በእግዚአብሔር ይቅር እንዲባልልን ምን ማድረግ አለብን?

**ለ7 ታሪክ 4**
**አንድ ላይ በግብፅ - ይህ ታሪክ ስለ እግዚአብሔር እቅድ ለህይወታችን የሚያወራ ነው፡፡**

| | |
|---|---|
| | **እየተማርን ያለነው፡**<br>• የሴፍ ከአባቱ ከያዕቆብ ጋር ዳግም ተገናኘ፡፡<br>• ሙሉ በሙሉ በእርሱ የምንታመን ከሆነ እግዚአብሔር ከመጥፎ ሁኔታዎች ውስጥ ጥሩውን ያወጣል፡፡<br>**ቁልፍ ጥቅስ፡ *ዘፍጥረት 50፡ 20***<br>**የመጽሐፍ ቅዱስ የንባብ ክፍል፡ *ዘፍጥረት 46፡ 1-34*** |
| አስተዋውቁ | ከልጆቹ መካከል አንዳቸው ቤት ቀይረው የሚያውቁ ከሆነ ጠይቋቸው፡፡ ከመካከላቸው ወደ ሌላ ሀገር መጓዝ የነበረባቸው አሉ? እንዴት ያለ ስራ የሚበዛበት ጊዜ ነው! እቃችሁን በሙሉ ስታሽጉ፡፡ ምን ተሰምቷቸው እንደነበር ልጆቹን ጠይቁ፡፡ ተጨንቀው ነበር ወይስ ጓጉተው ነበር? ያዕቆብና መላው ቤተሰቡ በግብፅ ውስጥ ወዳለው ወደ ጌሴም ምድር እንደሚጓዙ ልጆቹን አስታውሱ፡፡ |
| አስተምሩ | • ያዕቆብ (እስራኤል) እና መላው ቤተሰቡ ንብረታቸውን ሁሉ ያዙ፡፡ ከብቶቻቸውን ሰበሰቡና ወደ ግብፅ ጉዞ ጀመሩ፡፡ በመንገድም ሲሄዱ፣ አቁመው ለእግዚአብሔር መስዋዕት ወዳቀረቡበት ቤርሳቤህ ወደሚባል ስፍራ መጡ፡፡ *እግዚአብሔር እንደዛ ስለተንከባከባቸው በምስጋና ተሞልተው ነበር! **(ዘፍጥረት 46፡ 1)***<br>• እግዚአብሔር ያዕቆብን በህልም አናገረው፡፡ ያዕቆብ ግብፅ ሄዶ ለመኖር እንዳይፈራ ነገረው፡፡ በግብፅ እግዚአብሔር ያዕቆብን ሊባርከውና ቤተሰቡን ትልቅ ህዝብ ሊያደርግ ነበር፡፡ ከያዕቆብ ጋር እንደሚሆን ቃል ገባ፡፡ ***(ዘፍጥረት 46፡ 2-4)** እግዚአብሔር ሁሌም ቃሉን እንደሚጠብቅ ከልጆቹ ጋር ተወያዩ፡፡*<br>• ያዕቆብና ቤተሰቡ ከቤርሳቤህ ተነስተው ወደ ግብፅ መጡ፡፡ በጣም ብዙ ነበሩ፡፡ በአሁኑ ጊዜ በግብፅ በአጠቃላይ የያዕቆብ ቤተሰቦች 70 ነበሩ! ***(ዘፍጥረት 46፡ 5-27)***<br>• ሁሉም ወደ ጌሴም ምድር ሲደርሱ ዮሴፍ ሊገናኛቸው መጣ፡፡ ከዚህ ሁሉ አመት በኋላ አባቱን በማየቱ በጣም ተደስቶ ነበር፡፡ እጆቹን በአባቱ ዙሪያ አድርጎ ለረዥም ጊዜ አለቀሰ፡፡ ንጉስ ፈርኦን እንደመጡ ሰማ፡፡ በሰላም ተቀበላቸው እና በጌሴም ምድር አንድ ላይ እንዲኖሩ ፈቀደላቸው፡፡ ***(ዘፍጥረት 46፡ 28- 34)***<br>• *ይህንን አስደሳች ፍፃሜ ከልጆቹ ጋር ተወያዩ፡፡ ልክ እንደ ዮሴፍ እኛም በጥሩ እና በመጥፎ ጊዜያት በእግዚአብሔር ልንታመን እንደሚገባ አስረዱ፡፡ ሙሉ በሙሉ በእርሱ ከታመንን ከመጥፎ ሁኔታዎች ውስጥ ጥሩውን እንዲያወጣ በእግዚአብሔር መደገፍ እንችላለን፡፡*<br>**የመጽሐፍ ቅዱስ ጊዜ ትምህርቱን አጠናቁ፡፡**<br>**አሳዩ፡** FBI ዮሴፍ ከያዕቆብ ጋር ዳግም ተገናኘ፡፡ |
| አስጠኑ | ቁልፍ ጥቅሱን አስፈላጊ በሆነበት ቦታ ላይ አስተምሩና አስረዱ፡፡ ***ዘፍጥረት 50፡ 20*** ታሪኩን ለማጠቃለል ይህንን ጥቅስ ተጠቀሙ፡፡ ወንድሞቹ እንዴት ነበር ዮሴፍን ለመጉዳት የሞከሩት? እግዚአብሔር ይሄንን እንዴት ወደ መልካም አጋጣሚ ለወጠው? የእያንዳንዳችን ህይወት በእግዚአብሔር ቁጥጥር ስር መሆኑን ልጆቹ እንደገባቸው አረጋግጡ፡፡ |
| እዲታወስ | ታሪኩን ለመከለስ እንዲረዳ ልጆቹን ቀጥሎ ያሉትን ጥያቄዎች ጠይቋቸው፡፡.<br>• የያዕቆብ ቤተሰብ ወዴት ነበር ሚሄደው?<br>• መስዋዕት ለማቅረብ የት ጋር ነበር የቆሙት?<br>• እግዚአብሔር ለያዕቆብ ምን ምን ቃል ነው የገባለት?<br>• ጌሴም ሲደርሱ ማን ነው ሊገናኛቸው የመጣው?<br>• አሁን በግብፅ የሚኖሩ የያዕቆብ ቤተሰቦች ስንት ይሆናሉ?<br>• ይህ ታሪክ አሳዛኝ መጀመሪያ ነበረው፡፡ ደስ የሚል ፍፃሜ እንዲኖረው እግዚአብሔር እንዴት ነው የቀየረው? |

## <u>ለ8 ታሪክ 1</u>

**ኢየሱስ ያገኛቸው ሰዎች፡ የታመመችው ሴት - ይህ ታሪክ ስለ ጌታ ኢየሱስ ሃይል ነው፡፡**

<table>
<tr><td></td><td>እየተማርን ያለነው፡<br>• ኢየሱስ የእግዚአብሔር ልጅ ስለሆነ ሰዎችን ፈውሷል፡፡<br>• ጌታ ኢየሱስ በህይወታችን ውስጥ መልካም ነገሮችን ማድረግ ይችላል፡፡<br>ቁልፍ ጥቅስ፡ ሐዋ. ስራ 10፡ 38<br>የመጽሐፍ ቅዱስ የንባብ ክፍል፡ ሉቃስ 4፡ 38 - 44</td></tr>
<tr><td>አስተዋውቁ</td><td>ልጆቹ እንዲቆሙና የሚከተሉትን የሰውነት እንቅስቃሴዎች “በቦታው ላይ” እንዲያደርጉ ይጠይቁ - ለምሳሌ፡- መዝለል፣ ዱብ ዱብ፣ ፈጣን ሩጫ፣ መሰለፍ፣ እጅን በመጠቀም ፊት ለፊት አየሩን መምታት …. ወይንም ቦታው በቂ ከሆነ የትራፊክ መብራቶችን ጨዋታ መጫወት ይችላሉ፡፡ አንድ ቀለም ስትጠሩ ልጆቹ ትዕዛዙን ይፈፅማሉ - ቀይ = ቀጥ ብሎ መቆም፣ ብርቱካናማ = በቦታ ላይ መሮጥ፣ አረንጓዴ = መዞር፡፡ የትራፊክ መብራቶችን የማይታዘዙ ልጆች ከጨዋታው ይወጣሉ፡፡<br>በመጨረሻ በዚህ ሊደሰቱ የቻሉት ደህና እና ጤናማ ስለሆኑ እንደሆነ አስረዱ፡፡ ህመም ሲሰማን እና አልጋ ላይ መተኛት ሲኖርብን ግን አስደሳች አይደለም፡፡ በኢየሱስ ዘመን ብዙ የታመሙ ሰዎች ነበሩ ነገር ግን የሚረዱ ሀኪሞችም ሆኑ መድኃኒቶች አልነበሩም፡፡<br>በዚህ መግቢያ ላይ መሳተፍ ለማይችሉ ልጆች ተጠንቀቁ፡፡ እንደ አማራጭ፣ በዚህ ጊዜ ሀኪም መሆን እንዴት ሊሆን እንደሚችል አውሩ-ስለ ብዙ አይነት በሽታ ማወቅ፣ መድኃኒት ማዘዝ፣ የስራ መብዛት፣ አንዳንዴ መርዳት መቻል ነገር ግን አንዳንዴ አለመቻል፡፡ በዛሬው ታሪክ ውስጥ ከሁሉም በጣም ድንቅ ስለሆነው ሀኪም ስለ ጌታ ኢየሱስ! እንደምንማር አስረዱ፡፡</td></tr>
<tr><td>አስተምሩ</td><td>• ኢየሱስ ሰዎችን እያስተማረ በምኩራብ (አይሁዶች ስለ እግዚአብሔር ለመማር የሚሰበሰቡበት ስፍራ) ውስጥ ነበር፡፡ አንድ ሰውም ፈውሷል፡፡ አሁን ከሌሎች አንዳንድ ደቀመዛሙርት ጋር የስምኦንን ቤት የመጎብኛ ጊዜ ነበር፡፡ ግን አንድ ችግር ነበር፡፡ የስምኦን አማች (ይህ ምን ማለት እንደሆነ አስረዱ) በትኩሳት በጣም ታማ ነበር፡፡ ትኩሳቱ እንዴት አይነት ስሜት እንዲሰማት እንዳረገ አስረዱ - ከፍተኛ ሙቀትና ሙሉ ሰውነቷን ህመም፡፡ ስምኦን እና ሌሎቹም ኢየሱስ ሊፈውሳት እንደሚችል ያውቁ ነበር ስለዚህም እርዳታውን ጠየቁ፡፡ኢየሱስ ሊረዳቸው እንደሚችል እንዴት አሰቡ? (ሉቃስ 4፡ 38)<br><br>• ኢየሱስ ለመርዳት ፈቃደኛ ነበር፡፡ የሴቲቱን እጅ ነካና ትኩሳቱን አናገረው፣ ከዚያም እንድትነሳ ረዳት፡፡ በድንገት ተሻላትና ምግብ ማቅረብ ጀመረች፡፡ ከዚህ በፊት ምንም ችግር እንዳልነበረባት ሆነች! ሰዎቹ እርስ በእርስ ሊባባሉ የሚችሉትን አንዳንድ ነገሮች ልጆቹ እንዲያስቡ ጠይቋቸው፡፡ (ሉቃስ 4፡ 39)<br><br>• በዚያ ምሽት ጸሀይ በገባች ጊዜ ብዙ ሰዎች በሽታና ችግር ያለባቸውን ሌሎች ሰዎች ወደ ኢየሱስ አመጡ፡፡ በዚያ ሊሆኑ የሚችሉ ሰዎች ምን አይነት ሰዎች እንደሆኑና ለምን እንደመጡ አውሩ፡፡ በቀኑ መጨረሻ ኢየሱስ እንዴት አይነት ስሜት ተሰምቶት ይሆን? እንዴትም ቢመሽ እንኳን ኢየሱስ ግን ለሁሉም ሚሆን ጊዜ ነበረው፡፡ እጁን በእያንዳንዱ ላይ ጫነ፡፡ ሳይፈወስ የተመለሰ ማንም አልነበረም፡፡ በድጋሚ የሰዎቹን ምላሽ አስቡ፡፡ (ሉቃስ 4፡ 40)<br><br>• በሚቀጥለው ቀን ጠዋት ኢየሱስ ወደ አባቱ የሚጸልይበትን ጸጥ ያለ ስፍራ አገኘ፡፡ ነገር ግን ሰዎቹ አሁንም እሱን ፍለጋ መጡ! የእርሱን አስደናቂ ሀይል አውቀዋል፡፡ (ሉቃስ 4፡ 42)<br><br>• ዛሬም ጌታ ኢየሱስ ለሰዎች ያስባልና ሊረዳቸው ይፈልጋል፡፡ በእርሱ ለመታመን ፍቃደኞች ስንሆን በህይወታችን ውስጥ መልካም ነገሮችን ሊያደርግ ይችላል፡፡<br><br>የመጽሐፍ ቅዱስ ጊዜ ትምህርቱን አጠናቁ፡፡<br>አሳዩ፡ FBI ኢየሱስ በቅፍረናሆም ውስጥ ሲያድንና ሲፈውስ፡፡ (ገፅ 7 – 11)</td></tr>
<tr><td>አስጠኑ</td><td>ቁልፍ ጥቅሱን አስፈላጊ በሆነበት ቦታ ላይ አስተምሩና አስረዱ፡፡ ሐዋ. ስራ 10፡ 38 ከጥቅሱ ልጆቹ ሊይዙት የሚችሉትን ያክል ምረጡ፡፡</td></tr>
<tr><td>እዲታወስ</td><td>ታሪኩን ለመከለስ እንዲረዳ ልጆቹን ቀጥሎ ያሉትን ጥያቄዎች ጠይቋቸው፡፡.<br>• ኢየሱስ በምኩራብ ውስጥ ምን እያደረገ ነበር?<br>• ኢየሱስ የማንን ቤት ነበር የጎበኘው?<br>• ትኩሳት የነበረበት ማን ነበር?<br>• ኢየሱስ እርሷን ለመፈወስ ያደረጋቸው ሁለት ነገሮች ምን ነበሩ?<br>• ከተፈወሰች በኋላ ያደረገቻው ምን ነበር?<br>• ብዙ ሰዎች ወደ ኢየሱስ መምጣታቸውን የቀጠሉት ለምን ነበር?<br>• በሚቀጥለው ቀን ጠዋት ኢየሱስ ምን አስፈላጊ ነገር አደረገ?<br>• የጎደለውን ቃል ሙሉ "ኢየሱስ___________ እያደረገ ይዞር ነበር፡፡"</td></tr>
</table>

## <u>ለ8 ታሪክ 2</u>

**ኢየሱስን ያገኙ ሰዎች፡ ለምጻሙ ሰውዬ - ይህ ታሪክ ጌታ ኢየሱስ እንዴት እንደወደደን የሚያሳይ ነው፡፡.**

<table>
<tr><td></td><td>
እየተማርን ያለነው፡
<ul>
<li>ለምጻሙን ሰውዬ በመፈወስ ኢየሱስ ፍቅሩን አሳየ፡፡</li>
<li>ኢየሱስ ይወደናል እናም ህይወታችንን ሊቀይር ይፈልጋል፡፡</li>
</ul>
ቁልፍ ጥቅስ፡ ሉቃስ 7፡ 22<br>
የመጽሐፍ ቅዱስ የንባብ ክፍል፡ ሉቃስ 5፡ 12 -16
</td></tr>
<tr><td>አስተዋውቁ</td><td>
ይዟቸው ሊያውቅ ስለሚችል ተላላፊ በሽታ ልጆቹን ጠይቁ፣ ለምሳሌ፡- ኩፍኝ፣ ጉድፍ፡፡ ከሌሎች ርቀን መቆየት እንደሚኖርብ እና የሚያጓጓም ነገር ሊያመልጠን እንደሚችል አውሩ፡፡ በኢየሱስ ዘመን ለምጽ ከአንድ ሰው ወደ ሌላ ሰው የሚጋባ የተለመደ የቆዳ በሽታ እንደነበር አስረዱ፡፡ የያዛቸው ሰዎች ከቤተሰቦቻቸው ጋር መኖር ወይም ወደ ስራ መሄድ አይችሉም፡፡ ምንም መድኃኒት አልነበረም!<br>
አሁን ማግኘት ለምንችለው ለማንኛውም የጤና አገልግሎት እንዲያመሰግኑ ልጆቹን አበረታቱ - በጸሎት መግለፅ ትችላላችሁ፡፡
</td></tr>
<tr><td>አስተምሩ</td><td>
<ul>
<li>አንድ ቀን ከባድ ለምጽ ያለበት ሰው ወደ ኢየሱስ መጣ፡፡ በኢየሱስ ፊት ጉልበቱ ወድቆ እርዳታን ለመነ፡፡ “ጌታ ሆይ ፈቃደኛ ከሆንክ ልታነፃኝ ትችላለክ፡፡” አለ፡፡ ይህ ሰውዬ ኢየሱስ ፈቃደኛ ከሆነ እርሱን ለማንፃት ሀይል እንዳለው እንደሚያውቅ ያሳያል፡፡ ኢየሱስ ሰውዬውን ሊፈውሰው ፈቃደኛ ይሆን ወይስ አይሆን የሚለውን ገምቱ፡፡ ኢየሱስ ተላላፊ በሽታ ካለበት ሰው ጋር ማድረግ የሚፈልገው ነገር ይኖራል? (ሉቃስ 5፡ 12)</li>
<li>በእርግጥ ኢየሱስ ሰውዬውን ለመርዳት ፈልጎ ነበር፡፡ በጣም ይወደውና ምን ያህል እርዳታው እንመሚያስፈልገው ያውቅ ነበር፡፡ ከዚያ ኢየሱስ ድንቅ ነገር አደረገ፡፡ እጁን ዘርግቶ ሰውዬውን ዳሰሰውና “እኔ ፈቃደኛ ነኝ፡፡ ንፃ!” አለው፡፡ ኢየሱስ ሰውዬውን በመንካቱ ለምጽ አልያዘውም ነበር ነገር ግን ሰውዬው ወዲያውኑ ተሻለው፡፡ ቆዳው እንዴት ንፁህ እና ጤናማ እንደሆነ አስረዱ፣ በተጨማሪም ስለ ሰውዬው መደነቅ እና ምስጋና አውሩ፡፡ (ሉቃስ 5፡ 13) ይህ ሌላ ተአምራት ነበር፡፡ ኢየሱስ በህመም ላይ እና የሰዎችን ህይወት ለመለወጥ ያለውን ታላቅ ሀይል በድጋሚ አሳይቷል</li>
<li>መጽሐፍ ቅዱስ ኃጢአታችንን ከለምጽ ጋር ያነፃፀረዋል፡፡ ኃጢአት ምን እንደሆነ እና እንዴት ህይወታችንን እንደሚያበላሽ አውሩ፡፡ የሰራናቸው ስህተቶች ቢኖሩም እንኳን ጌታ ኢየሱስ ግን ይወደናል፡፡ ፍቃደኛ ከሆንን ይቅር ሊለንና ከኃጢአታችንም ሊያነፃን ይችላል፡፡ ውስጠ ህይወታችን ሊቀየር ይችላል፡፡</li>
<li>ኢየሱስ ሰውዬውን ከፈወሰው በኋላ ሄዶ መፈወሱን ለካህን እንዲያሳይ ነገረው፡፡ ከዚህ በኋላ ህይወቱ እንዴት የተለየ ሊሆን ይችላል? ሰውዬው ኢየሱስን ያገኘበትን ቀን መቼም ቢሆን አይረሳውም፡፡ (ሉቃስ 5፡ 14) ኃጢአታችንን ይቅር እንዲል ጌታ ኢየሱስን ከጠየቅነው ለእኛም የህይወታችን ምርጡ ቀን ይሆንልናል፡፡</li>
</ul>
የመጽሐፍ ቅዱስ ጊዜ ትምህርቱን አጠናቁ፡፡<br>
አሳዩ፡ የሚሆን ስዕል በFBI ላይ የለም፡፡
</td></tr>
<tr><td>አስጠኑ</td><td>
ቁልፍ ጥቅሱን አስፈላጊ በሆነበት ቦታ ላይ አስተምሩና አስረዱ፡፡ ሉቃስ 7፡ 22 ይህ ጥቅስ ጌታ ኢየሱስ የሰዎችን ህይወት የሚለውጥበትን ስድስት መንገዶች ይዘረዝራል፡፡ ሁሉንም በቅደም ተከተል ማግኘት ከባድ ሊሆን ይችላል - ለእያንዳንዱ ሀረግ አንድ ቀላል እንቅስቃሴ ለመጠቀም ይሞክሩ ለምሳሌ፡- አይነ ስውር= ወደ አይን ጠቁሙ፣ አንካሳው ተራመደ= በቦታ ላይ ተራመዱ፣ ለምፅ ያለባቸው= በእጅ መዳፍ ላይ ያለውን ቆዳ ይንኩ፡፡ እንደአማራጭ፣ ለመናገር በጣም ረዥም ከሆነ ለተለያዩ ቡድኖች ወደ ሀረጎች ከፋፍሉት፡፡ ጥሩ የመጽሐፍ ቅዱስ እውቀት ያላቸው የደረጃ 2 ልጆች ከእያንዳንዱ ምድብ ኢየሱስ የፈወሳቸውን ሰዎች ምሳሌ መስጠት ይችላሉ፡፡
</td></tr>
<tr><td>እዲታወስ</td><td>
እነዚህን አረፍተ ነገሮች ለእውነት/ሀሰት ፈተና ተጠቀሚቸው፡፡
<ul>
<li>ለምጽ ተላላፊ በሽታ ነው፡፡</li>
<li>ሰውዬው ከቤተሰቦቹ ጋር እንዲሆን ብቻ ነበር የሚፈቀድለት፡፡</li>
<li>በኢየሱስ ፊት በጉልበቱ ወድቋል፡፡</li>
<li>ኢየሱስ ሊፈውሰው እንደሚችል ሰውየው እርግጠኛ አልነበረም፡፡</li>
<li>ኢየሱስ ዳስሶታል፡፡</li>
<li>ኢየሱስ የእግዚአብሔር ልጅ ስለሆነ ሊፈውሰው ችሏል፡፡</li>
<li>ከትንሽ ደቂቃዎች በኋላ ተሻለው፡፡</li>
<li>ሄዶ ራሱን ለካህን ማሳየት ነበረበት፡፡</li>
<li>ሁላችንም ኃጢአት የሚባል በሽታ አለብን፡፡</li>
<li>ጌታ ኢየሱስ ይወደናል እና ኃጢአታችንን ይቅር ሊለን ፍቃደኛ ነው፡፡</li>
</ul>
</td></tr>
</table>

## ለ8 ታሪክ 3

**ኢየሱስን ያገኙ ሰዎች - ምንም ረዳት የሌለው ሰው - ይህ ታሪክ ጌታ ኢየሱስ እንዴት ይቅር እንደሚል የሚያሳይ ነው።**

| | |
|---|---|
| | **እየተማርን ያለነው:**<br>• ኢየሱስ ሽባውን የመፈወስ ብቻ ሳይሆን ኃጢአቱንም ይቅር የማለት ሃይል ነበረው።<br>• ኢየሱስ ኃጢአታችንን ይቅር የማለት ሃይል አለው።<br><br>**ቁልፍ ጥቅስ:** ***ሉቃስ 5፡ 24***<br>**የመጽሐፍ ቅዱስ የንባብ ክፍል:** ***ሉቃስ 5፡ 17 - 26*** |
| አስተዋውቁ | በትምህርት ቤት ውስጥ ጓደኛቸውን ወይም በቤት ውስጥ ለመርዳት ምን ለማድረግ እንደሚችሉ ሀሳብ እንዲያቀርቡ ልጆቹን ጠይቁ።ለመርዳት ዝግጁ ስለመሆናቸው አመስግኗቸው። በዛሬው ታሪክ አራት ጓደኞቸ መራመድ የማይችለውን ጓደኛቸውን ወደ ጌታ ኢየሱስ ተሸክመው ወሰዱት። ከተቻለ እንዴት ይሄን እንዳረጉ በተግባር ለማስረዳት ምንጣፍ ይኑራችሁ። ለምን ወደ ኢየሱስ አመጡት? አዎ፣ ኢየሱስ ጓደኛቸውን ለመፈወስ ሀይል እንደነበረው ያውቁ ነበር። |
| አስተምሩ | • ነገር ግን ወደ ኢየሱስ መድረስ እንደጠበቁት ቀላል አልነበረም። ብዙ ሰዎች ኢየሱስን ለመስማት ቤት ውስጥ ጥቅጥቅ ብለው ነበር። *የኢየሱስን ቃል ለመስማት መፈለግ ለእኛም ጠቃሚ ነው።* በበር ውስጥ መግባት የማይታሰብ ነገር ነበር ስለዚህ ሰውዬውን ተሸክመው ከቤቱ ጎን ባለው ደረጃ ወጥተው ወደ ጣራው ወጡ። ሊረዳቸው የሚችለው ኢየሱስ ብቻ ስለነበረ በቀላሉ ተስፋ አልቆረጡም! *ቤት ውስጥ ከታች ቆመው ለነበሩት ሰዎች ጣራው ላይ ቀዳዳ ሲታይ እና ሰውዬውን በጥንቃቄ ወደ ኢየሱስ እግር ፊት ሲያወርዱት እንዴት ሆኖ ሊሆን እንደሚችል በአይምሮአቸው እንዲስሉት ልጆቹን ጠይቋቸው።*<br>***(ሉቃስ 5፡ 18 – 19)***<br><br>• *ኢየሱስ ሰውዬውን እንዴት ሊፈውሰው ይችላል? የጴጥሮስ አማችና የለምፃሙ ታሪክ ውስጥ እንዴት እንደፈወሰ እንዲያስታውሱ ልጆቹን ጠይቁ።* ነገር ግን በዛሬው ታሪክ፣ ኢየሱስ ሰውዬውን አናገረውና "ወዳጄ ኃጢአትህ ይቅር ተብሎልኃል።" አለው። ቤት ውስጥ የነበሩት አንዳንድ ሰዎች ተናደዋለ ምክንያቱም ኢየሱስ ኃጢአትን ይቅር ማለት እንደሚችል አያምኑም ነበር። እግዚአብሔር ብቻ ኃጢአትን ይቅር ማለት እንደሚችል ነበር ያሰቡት እና ኢየሱስ የእግዚአብሔር ልጅ እንደነበር አላመኑም። ምን እያሰቡ እንደነበር ኢየሱስ አውቋል። *የእኛንም ሀሳብ ያውቃል! **(ሉቃስ 5፡ 20 -24)***<br><br>• የሰውዬውን ህይወት ማየት ባይችሉም እንኳን የምር ግን ኃጢአቱን ይቅር እንዳለው ሊያረጋግጥላቸው ፈልጎ ነበር! ስለዚህ ራሱን መርዳት የማይችለውን ሰውዬ እንዲነሳና አልጋውንም ይዞ ወደቤቱ እንዲሄድ ነገረው። በፍጥነት ሰውዬው ይህንን አደረገና እግዚአብሔር እያመሰገነ ሄደ! ሁሉም ተደንቆ ነበር። የኢየሱስ ሀይል የሰውዬውን እግር መፈወስ ብቻ ሳይሆን ነገር ግን ኃጢአቱንም ይቅር ማለት ይችላል! ሌላ ማንም እንዲህ አይነት ሀይል የለውም! ***(ሉቃስ 5፡ 24 – 26)***<br><br>• ትልቁ ፍላጎታችን ኃጢአታችን ይቅር መባሉ ነው። *ልጆቹ በታሪክ 2 የተማሩትን ከልሱ - ኃጢአት ምን እንደሆነ፣ ከእግዚአብሔር ጋር ያለንን ግንኙነት ኤዴት እንደሚያበላሽ እና ከመንግስተ ሰማያት እንደሚያስቀረን።* ጌታ ኢየሱስ ኃጢአታችንን ይቅር የማለት ሀይል አለው ምክንያቱም ራሱ ምንም ኃጢአት የለበትም። የኃጢአታችንን ቅጣት ለመውሰድ በመስቀል ላይ ለመሞት ፍቃደኛ ነበር። ለኃጢአታችን ከልባችን ልንጸጸት እና ይቅር የምንባልበትን መንገድ ስላዘጋጀልን ጌታ ኢየሱስን ልናመሰግነው ይገባል።<br><br>**የመጽሐፍ ቅዱስ ጊዜ ትምህርቱን አጠናቁ::**<br>**አሳዩ:** FBI ሽባው ሰውዬ በጣራው በኩል ሲወርድ። |
| አስጠኑ | የታሪኩ ክፍል የሆነውን ቁልፍ ጥቅሱን አስተምሩ። ***ሉቃስ 5፡ 24*** "የሰው ልጅ" የጌታ ኢየሱስ ሌላ መጠሪያ እንደሆነ አስረዱ። |
| እዲታወስ | ታሪኩን ለመከለስ እንዲረዳ ልጆቹን ቀጥሎ ያሉትን ጥያቄዎች ጠይቋቸው።.<br>• ሰውዬው ስንት ጓደኞች ነበሩት?<br>• ሰውዬው ምን ነበር ችግሩ?<br>• ጓደኛቸውን ኢየሱስ ጋር ማድረስ ለምን ከባድ ሆነ?<br>• እንዴት ቤቱ ውስጥ ገቡ?<br>• ኢየሱስ ሰውዬውን መጀመሪያ ምን ነበር ያለው?<br>• አንዳንድ ሰዎች ለምን ነበር የተናደዱት?<br>• ኢየሱስ የሰውዬውን ኃጢአት ይቅር ማለቱን እንዴት አሳየ?<br>• ጌታ ኢየሱስ ሊያደርግልን የሚችለው በጣም ጠቃሚው ነገር ምንድን ነው? |

## <u>ለ8 ታሪክ 4</u>
## ኢየሱስን ያገኙ ሰዎች፡ ማቴዎስ - ይህ ታሪክ ጌታ ኢየሱስን ስለመከተል ነው፡፡

**እየተማርን ያለነው፡**

- የማቴዎስ ህይወት እንዴት እንደነበር ኢየሱስ ያውቃል ቢሆንም ግን እንዲከተለው ፈልጎ ነበር፡፡
- ኢየሱስ እንድንከተለው ይፈልጋል፡፡

**ቁልፍ ጥቅስ፡ *ሉቃስ 5፡ 32***
**የመጽሐፍ ቅዱስ የንባብ ክፍል፡ *ሉቃስ 5፡ 27 - 32***

### አስተዋውቁ

መስራት ስለሚፈልጉት አይነት ስራ ከልጆቹ ጋር ውይይት አድርጉ፡፡ እነዚህን ስራዎች መስራት ምን ጥሩ ነገር እንዳለው ገምግሙ፡፡
***<u>ወይም</u>***
ቀላል እንቅስቃሴዎችን በመጠቀም በማህበረሰቡ ውስጥ የተለመዱ ስራዎችን አሳዩና ልጆቹ ምን እንደሆነ ይገምቱ፡፡ የዛሬው ታሪክ ቀራጭ ስለነበረው ማቴዎስ (ሌዊ) ስለሚባል ሰው እንደሆነ አስረዱ፡፡
ከመንገድ ዳር ተቀምጦ ሀገሪቱን ለሚቆጣጠሩት ለሮማውያኑ ለመስጠት ከሰዎች ግብር ይሰበስባል፡፡ አሁንም ግብርን የመክፈላችንን እውነታ እና እነርሱ የለመዱትን ነገር መጥቀስ ይችላሉ፡፡
እንደ አለመታደል ሆኖ ማንም ማቴዎስን አይወደውም ነበር፡፡ ግብር ሰብሳቢዎች ለጠላት (ሮማውያን) ስለሰሩ ብቻ ሳይሆን ነገር ግን አንዳንድ ጊዜ መውሰድ ካለባቸው ገንዘብ በላይ ስለሚወስዱና ለራሳቸው ስለሚያደርጉ ይጠሉ ነበር፡፡

### አስተምሩ

- *አንድ ቀን ማቴዎስ ስራውን ሲሰራ ኢየሱስ አየው፡፡ ኢየሱስ ስለ ማቴዎስ ምን እንዳሰበ ገምቱ - ማቴዎስ ምን አይነት ሰው እንደነበር ያውቅ ነበር? አዎ በእርግጥም ... ስለእያንዳንዳችን ሁሉንም ነገር ያውቃል፡፡ ኢየሱስ ከማቴዎስ ጋር ማድረግ የሚፈልገው ነገር ይኖር ይሆን? አዎ! ኢየሱስ ሊረዳ የመጣው ልክ እንደ ማቴዎስ አይነት ሰው ነበር - የማቴዎስን ህይወት መቀየር ይችላል!* ስለዚህ ከማቴዎስ አጠገብ ቆመና፣ "ተከተለኝ፡፡" አለው፡፡ ***(ሉቃስ 5፡ 27)*** *ማቴዎስ ምን ያደርግ ይሆን? ማቴዎስ መምረጥ የነበረበትን ምርጫ አቅርቡ፡፡*

- *ማቴዎስ ምን ማድረግ እንደሚፈልግ በፍጥነት አውቆ ነበር፡፡ ኢየሱስን መከተል ነበር! ኢየሱስ እርሱን መጥራቱ እንዴት ሚደንቅ ነው! ተነሳ፣ ሁሉንም ነገር ተወና ከኢየሱስ ጋር ሄደ፡፡* ***(ሉቃስ 5፡ 28)*** *ጌታ ኢየሱስ፣ እንድንከተለውና በህይወታችን እንድናኖረው እያንዳንዳችንን እንደሚጠራን አስረዱ፡፡ እኛም ምርጫ መምረጥ አለብን፡፡*

  ማቴዎስ ጓደኞቹ ኢየሱስን እንዲያገኙና ህይወቱ እንዴት እንደተቀየረ ሊያሳውቃቸው ይፈልግ ነበር፡፡ ስለዚህ ከኢየሱስና ከደቀመዛሙርቱ ጋር በቤቱ እራት ላይ እንዲገኙ ጋበዛቸው፡፡ በዚያ የነበሩ አንዳንድ ሰዎች፣ ኢየሱስ ከማቴዎስና ከጓደኞቹ ጋር በመደባለቁ ስህተት እንደነበረ አሰቡ፡፡ ኢየሱስ ከኃጢአተኞች ይልቅ ከጥሩ ሰዎች ጋር ብቻ ጊዜ ማሳለፍ እንዳለበት ነበር የሚያስቡት፡፡ ሁሉም ሰው ኃጢአተኛ እንደሆነ አላስተዋሉም ነበር፡፡ ለምን ወደ ምድር እንደ መጣ ኢየሱስ አስረዳቸው - ህይወታቸው ጥሩ እንደሆነ ለሚያስቡ ሰዎች ሳይሆን፣ ነገር ግን ኃጢአት መስራታቸውን ለሚያውቁ እና በኃጢአታቸው ለሚጸጸቱት ሰዎች ነው፡፡ ***(ሉቃስ 5፡ 29 – 32)***
  ኢየሱስ ኃጢአትን አይወድም ነገር ግን እንደ ማቴዎስ እና እንደ እኛ ያሉ ኃጢአተኞችን ይወዳል! እኛም እርሱን መከተልና ለይቅርታ እርሱን ማመን አለብን፡፡
- በኋላ ላይ፣ በጣም አስፈላጊ ስራ እንዲሰራ እግዚአብሔር ማቴዎስን መረጠው፡፡ የአዲስ ኪዳንን መጽሐፍ ፃፈ፡፡ ኢየሱስን ለመከተል እና በህይወቱ ውስጥ ያሉ ስህተቶችን እንዲያስተካክልለት የወሰነበት ቀን እንዴት ድንቅ ነበር፡፡

**የመጽሐፍ ቅዱስ ጊዜ ትምህርቱን አጠናቁ፡፡**
**አሳዩ፡** FBI ኢየሱስ ቀራጩን ማቴዎስን ደቀመዝሙሩ እንዲሆን ጠራው፡፡

### አስጠኑ

ቁልፍ ጥቅሱን አስፈላጊ በሆነበት ቦታ ላይ አስተምሩና አስረዱ፡፡ ***ሉቃስ 5፡ 32*** ከባድ የሆኑ ቃላትን በማስረዳት
- ለምሳሌ፡ ፅድቅ እና ንስሀ፡፡

### እዲታወስ

በክፍል ውስጥ ልጆቹ፣ ኢየሱስ በእነዚህ ታሪኮች ውስጥ ያገኛቸውን የተለያዩ ሰዎች ስዕሎችን መደርደር ይችላሉ፡፡ <u>ወይም ደግሞ</u> በ ለ8 ላይ በመመስረት መምህሩ የመረጧቸውን ያለፉት ትምህርቶች ጥያቄዎችን በመጠቀም የክለሳ ፈተና መፈተን ትችላላችሁ እና ትንሽ ስለ ማቴዎስ ጨምሩ፣ ለምሳሌ ፡-

- የማቴዎስ ስራ ምን ነበር?
- ኢየሱስ ለማቴዎስ ምን ነበር ያለው?
- ማቴዎስ ኢየሱስን ከተከተለ በኋላ ምን ነበር ያደረገው?

## <u>ለ9 ታሪክ 1</u>

**የሙሴ መወለድ - ይህ ታሪክ እግዚአብሔር እንዴት እንደሚጠነቀቅ የሚያሳይ ነው።**

<table>
<tr><td></td><td>እየተማርን ያለነው፡<ul><li>እግዚአብሔር ለሙሴ ተጠንቅቋል እና ለእኛም ይጠነቀቃል። (ደረጃ 1)</li><li>እግዚአብሔር ለእኛ ህይወት እቅድ እንዳለው ሁሉ ለሙሴ ህይወትም እቅድ ነበረው። (ደረጃ 2)</li></ul>ቁልፍ ጥቅስ፡ ዕብራውያን 11፡ 23<br>የመጽሐፍ ቅዱስ የንባብ ክፍል፡ ዘጸአት 2፡ 1 - 10</td></tr>
<tr><td>አስተዋውቁ</td><td>እግዚአብሔር ለእያንዳንዳችን ህይወት እቅድ እንዳለው አስረዱ። የተወለድንባቸው ቤተሰቦች እና በእኛ ላይ የሚደርሱት ነገሮች ዝም ብለው የሚሆኑ ነገሮች አይደሉም - ይልቁን እግዚአብሔርን እንድናገለግለው ሊያዘጋጀን ይጠቀምባቸዋል። በእነዚህ ታሪኮች ውስጥ ስለ ሙሴ እንማራለን። እግዚአብሔር ለሙሴ፣ ሲያድግ የሚሰራው በጣም አስፈላጊ ስራ ነበረው። ዛሬ እግዚአብሔር ሙሴን በልጅነቱ እንዴት እንደጠበቀው እንማራለን። የሙሴ ታሪክ በመጽሐፍ ቅዱስ በሁለተኛው መጽሐፍ ውስጥ ይገኛል። የዚህን መጽሐፍ ስም የሚያውቅ ካለ ጠይቁ እና የት እንደሚገኝ አሳዩአቸው።<br>እንደ አማራጭ፣ ይህንን ታሪክ ለደረጃ 1 ህፃናት የምታስተምሩ ከሆነ ስለ አራስ ህፃናት ማውራት።</td></tr>
<tr><td>አስተምሩ</td><td><ul><li>እስራኤላውያን (ዕብራውያን) ባሪያ የሆኑበትን መነሻ በአጭሩ አስረዱ - የደረጃ 2 ትምህርትን መግቢያ ይመልከቱ። (ዘጸአት 1፡ 1-11) ንጉስ ፈርኦን የእስራኤላውያን ቁጥር መጨመርን ለማስቆም ከመፈለጉ የተነሳ ሁሉም እስራኤዊ ወንድ ህፃናት ወደ አባይ ወንዝ እንዲጣሉ ወሰነ። (ዘጸአት 1፡ 22) አንድ እስራኤላዊ እናት እና አባት አዲስ ወንድ ልጅ ቢወልዱ ምን ይሰማቸው ነበር?</li><li>አንድ ቤት ውስጥ፣ የሚያምር ጤነኛ ወንድ ልጅ ተወልዶ ነበር። እግዚአብሔር እንዲጠብቀው በማመን ወላጆቹ ቤት ውስጥ ደበቁት። ነገር ግን ከሶስት ወር በኋላ ሊደብቁት አልቻሉም ነበር። ለምን? እናቱ ከቄጤማ (አስረዱ) ውኃ የማያስገባ ቅርጫት ሰራች፣ ልጁን ውስጡ አስቀመጠችና ቅርጫቱን በወንዙ ዳርቻ ላይ ባሉት ረጃጅም ቄጤማ መሀል ደበቀችው። ማርያም፣ የልጁ እህት የሚፈጠረውን ነገር ለማየት እዚያ ቀረች ነገር ግን እግዚአብሔር ብቻ ነበር ልጁን መጠበቅ የሚችለው። (ዘጸአት 2፡ 1 – 4)</li><li>የታሪኩን ቀጣይ ክፍል በትዕይንት መልክ ተናገሩ - ልዕልቷ (የፈርኦን ሴት ልጅ) እና ረዳቶቿ አብረው ሲመጡ ማርያም እንዴት እንዳስተዋለች ግለፁ። ልጁን ታየው ይሆን? ለንጉሱ ትነግረው ይሆን? አዎ፣ ልዕልቷ ቅርጫቱን አየችው እና ወደ እሷ እንድታመጣው ረዳቷን ጠየቀቻት። ዕብራዊውን ህፃን ውስጡ ስታየው የነበራትን ምላሽ ግለፁ። ልዕልቷ እንዲጎዳ አትፈቅድም! የህፃኑን ደህንነት በመጠበቅ እግዚአብሔር በስራ ላይ ነበር! (ዘጸአት 2፡ 5 – 6)</li><li>ከዛም ማሪያም ወደፊት ሄዳ ለልጁ ሞግዚት ለማግኘት ጥያቄ አቀረበች። ማንን ታገኝ ይሆን? ልዕልቷ ተስማማች እና ማሪያም የራሷን እናት ለማግኘት ሮጠች! ስለዚህ የልጁ እናት በቤት በሙሉ ደህንነት እሱን መንከባከብ ቻለች ምክንያቱም ልዕልቷ ተስማምታለች።በኋላ ላይ ልጁ ሲያድግ በፈርኦን ቤተመንግስት ውስጥ እንዲኖር ልዕልቷ ወሰደችው። ወሰደችውና ሙሴ ብላ ጠራችው፣ "ከውኃ የወጣ" ማለት ነው። (ዘጸአት 2፡ 7-10) አሁን ሙሴ የግብፅ ልዑል ሆኖ ነበር!</li><li>እግዚአብሔር ከተፈጠረው ነገር ሁሉ ጀርባ እንደነበር ልጆቹ እንዲገባቸው አድርጉ። በፈርኦን ህግ መሰረት ልጁ መሞት ነበረበት። የሙሴ ወላጆች በእግዚአብሔር እምነት ነበራቸው - ልጃቸውን እንዲጠብቅ እግዚአብሔርን አምነው ነበር እርሱም ጠበቀው። ይሄ የእግዚአብሔር እቅድ የመፈጸሙ ጅማሬ ብቻ ነበር። እግዚአብሔር በህይወታችን ውስጥ ፍቃዱን እንዲፈፅም እንድንታመነው ይፈልጋል።</li></ul>የመጽሐፍ ቅዱስ ጊዜ ትምህርቱን አጠናቁ።<br>አሳዩ፡ FBI ህፃኑ ሙሴ።</td></tr>
<tr><td>አስጠኑ</td><td>ቁልፍ ጥቅሱን አስፈላጊ በሆነበት ቦታ ላይ አስተምሩና አስረዱ። ዕብራውያን 11፡ 23 (ደረጃ 2) ደረጃ 1 ህፃናት የመጀመሪያውን አረፍተ ነገር መማር ይችላሉ።</td></tr>
<tr><td>እዲታወስ</td><td><ul><li>የሙሴ ታሪክ የትኛው መጸሐፍ ላይ ነው የሚገኘው?</li><li>ፈርኦን ሁሉንም የዕብራውያን ወንድ ህፃናት ምን ለማድረግ ነበር የወሰነው?</li><li>ህፃኑ ምን ያህል ጊዜ ነበር ቤት ውስጥ የተደበቀው?</li><li>እናቱ ምን ነበር የሰራቸው?</li><li>ህፃኑን የት ነበር ያስቀመጠችው?</li><li>ለማየት ወንዙ ጋር የቆየው ማን ነበር?</li><li>ማን ነበር ልጁን ያገኘው?</li><li>ከዚያ በኋላ የሙሴ ህይወት ለምን ነበር አደጋ ውስጥ ያልሆነው?</li><li>በታሪኩ ውስጥ ማን ነበር እምነት ያሳየው?</li><li>ማን ነበር ሙሴን በደህና የያዘው?</li></ul></td></tr>
</table>

## ሰ9 ታሪክ 2

**የሙሴ ትልቅ ስህተት - ይህ ታሪክ የተሻለ ነው ብለን ያሰብነውን ነገር ስለማድረግ ነው፡፡**

**እየተማርን ያለነው፡**

- ሙሴ በጣም በፍጥነት በቁጣ እርምጃ ሲወስድ ስህተት ሰራ፡፡
- መጥፎ ነገር ማድረግ ከሚያስከትለው መዘዝ ማምለጥ አንችልም፡፡

**ቁልፍ ጥቅስ፡ *ዘጸአት 2፡ 11 - 15***
**የመጽሐፍ ቅዱስ የንባብ ክፍል፡ *ዘኁልቁ 32፡ 23***

### አስተዋውቁ

አንዳንድ ጊዜ እኛ የተሻለ እናውቃለን ብለን እናስባለን፡፡ አንድ አዋቂ ለአንድ ልጅ እንዴት እንደሚሰራ ሊያሳየው የሚችለውን ነገር ምሳሌ ምረጡ፣ ልጁ ግን በራሱ መንገድ ይሰራዋል እና ነገሩ በትክክል አይሰራም!

ባለፈው ሳምንት ስለ ሙሴ ተምረናል፡፡ *ለማስታወስ አንዳንድ ጥያቄዎችን ጠይቁ፡፡* ሙሴ ልጅ እያለ የት ለመኖር ነበር የሄደው? የራሱ ሰዎች ምን ተብለው ነበር የሚጠሩት? (እስራኤላውያን/ዕብራውያን)፡፡ ባሪያ እንደነበሩና በግብፃውያኑ እንዴት በጭካኔ እንደተገዙ ልጆቹን አስታውሷቸው፡፡ በበዛሬው ታሪክ ሙሴ አድጓል፡፡ ሙሴ የተሸለ አውቃለው ብሎ ያሰበበትን ሁኔታ ለማወቅ በጥንቃቄ አዳምጡ፡፡

### አስተምሩ

- አንድ ቀን ሙሴ የራሱን ህዝብ ለመጎብኘት ሄደ፡፡ በድንገት ከመካከላቸው አንዱ በግብፃዊ እየተመታ አየ፡፡ *ሙሴ እንዴት አይነት ስሜት ተሰምቶት ይሆን? (ቁጣ፣ ህዝቡን ለመከላከል መፈለግ)፡፡* በፍጥነት ሙሴ ማንም እያየ እንዳልሆነ ዞር ዞር ብሎ ተመለከተና ከግብፅ የሆነውን ሰውዬ ገደለው፡፡ ከዛም ሬሳውን አሸዋ ውስጥ ደበቀው፡፡ ሙሴ ትክክለኛ ነገር እንዳደረገ አሰበ፣ ግን *የሙሴ ድርጊት በጣም የተሳሳተ እንደነበር ልጆቹ ማየት እንዲችሉ አድርጉ፡፡ (ደረጃ 2፡ በተጨማሪም እግዚአብሔር የግብፃውያኑን መጥፎ ስራ እንዴት እንዳየ እና ወደፊት ሁሉንም ጥፋቶች እንዴት እንደሚቀጣ መጥቀስ ይችላሉ፡፡) ሙሴ ከሰራው ጥፋት የሚያመልጥ ይመስልዎታል? ካልሆነ ለምን? **ዘጸአት 2፡ 11 – 12)***

- በቀጣዩ ቀን ሙሴ ሁለት ዕብራውያን ሲጣሉ አየ፡፡ ምን እየተፈጠረ እንደሆነ ሲጠይቅ፣ አንዱ ሰውዬ "እኛ ላይ ለመፍረድ አንተ ማን ነህ? ግብፃዊውን እንዳደረከው እኔን ለመግደል እያሰብክ ነው?" አለው፡፡ አሁን ሙሴ ግብፃዊውን ሲገድል እንደታየ አውቆ ነበር፡፡ *አሁን ምን ተሰምቶት ይሆን? (ንጉሱ ይሰማል ብሎ መፍራት)* ብዙም ሳይቆይ ፈርኦን ሙሴ ምን እንዳደረገ ሰማ እና ሊገድለው ፈለገ፡፡ ሙሴ ለህይወቱ ምድያም ወደሚባል  ዮቶር ለሚባል ሰውዬ እንደ እረኛ ሆኖ ወደሰራበት ወደ ሌላ ሀገር መሸሽ ነበረበት፡፡ ***(ዘጸአት 2፡ 13 – 15)***

- ሙሴ ስለ ሰራው ስህተት እግዚአብሔርም ያውቅ ነበር፡፡ *እግዚአብሔር እንዴት የምናደርገውን ነገር ሁሉ እንደሚያይና ስህተታችንን ከእርሱ መደበቅ እንደማንችል አውሩ፡፡* ሙሴ ትልቅ ሰው ቢሆንም እንኳን ጥፋት አጥፍቷል እና ትክክለኛውን ነገር አላደረገም፡፡ መሪ ለመሆን ዝግጁ ከመሆኑ በፊት ገና ብዙ መማር ያለበት ነገር ነበር፡፡ ከሙሴ ጥፋት መማር እና እርሱን የሚያስደስተውን ትክክለኛ ነገር እንድናደርግ እንዲረዳን እግዚአብሔር ላይ መደገፍ አለብን፡፡

**የመጽሐፍ ቅዱስ ጊዜ ትምህርቱን አጠናቁ፡፡**
**አሳዩ፡FBI:** ሙሴ እንደ ግብፅ ልዑል፡፡

### አስጠኑ

ቁልፍ ጥቅሱን አስፈላጊ በሆነበት ቦታ ላይ አስተምሩና አስረዱ፡፡ ***ዘኁልቁ 32፡ 23*** ጥቅሱን ከሙሴ ስህተት ጋር አገናኙት፡፡ የሙሴ ኃጢአት ምን ነበር? እንዴት ነበር የታወቀበት? ከልጆቹ ተሞክሮ ጋር ተያያዥነት ስላለው ሁኔታ የተወሰነ ምሳሌ መስጠትም ትችላላችሁ፡፡

### እዲታወስ

እነዚህን እውነት/ሀሰት አረፍተ ነገሮች እንደ ፈተና ተጠቀሟቸው፡

- ሙሴ እስራኤላዊ ነው የገደለው፡፡
- ማንም ያላየው መስሎት ነበር፡፡
- ሌላ ዕብራዊ ሰው አይቶት ነበር፡፡
- ምን እንደተፈጠረ እግዚአብሔር አይቶ ነበር፡፡
- ፈርኦን ሙሴን እስር ቤት አስገባው፡፡
- ሙሴ መሪ ለመሆን ዝግጁ ከመሆኑ በፊት ብዙ ነገር መማር ይቀረው ነበር፡፡

**ለ9 ታሪክ 3**
**ሙሴ የሚቃጠል ቁጥቋጦ አየ - ይህ ታሪክ ለእግዚአብሔር ለመስራት ዝግጁ ስለመሆን ነው፡፡**

| | |
|---|---|
| | **እየተማርን ያለነው፡**<br>• እግዚአብሔር ቅዱስ ነው እና ይሄንን ሁሌ ማስታወስ አለብን፡፡<br>• ሙሴ እንቢተኛ መሪ ነበር ነገር ግን እግዚአብሔር ሲረዳው ቃል ገባለት፡፡<br><br>**ቁልፍ ጥቅስ፡** ***ዘጸአት 3፡ 12***<br>**የመጽሐፍ ቅዱስ የንባብ ክፍል፡** ***ዘጸአት 3 – 4፡ 17*** |
| አስተዋውቁ | አንድ አስፈላጊ እና አስደሳች ነገር ለመስራት ስለመጠየቅ አውሩ፣ ለምሳሌ፡-እናንተ ቡድን ውስጥ ላሉት ልጆች ተገቢ የሆነ ሀላፊነት እንድትሰሩት ስትጠየቁ ምን ተሰማችሁ? *(ፍርሀት / ሌላ ሰው ቢጠየቅ ብላችሁ መመኘት?)*<br>የዛሬው ታሪክ የሆነው ከሙሴ ትልቅ ስህተት ከ40 አመታት በኋላ ነው፡፡ ሙሴ ለ40 አመታት በበረሀ እረኛ ሆኖ ነበር፡፡ እግዚአብሔር አልረሳውም፡፡ ይቅር ሲለው ፍቃደኛ ነበር እና አሁን ለእርሱ እንዲሰራው በጣም ልዩ ስራ ነበረው፡፡ |
| አስተምሩ | • እስከዚህ ቀን ድረስ ሁሉም ቀን በብዛት ተመሳሳየ ነበር፣ … ሙሴ የሚቃጠል ቁጥቋጦ ተመለከተ፡፡ እንግዳው ነገር ምንም እንኳን ነበልባሉ ቢኖርም ቅጠሎቹና ቅርንጫፎቹ አልተቃጠሉም ነበር! ሙሴ ለማየት ቀረብ አለ ከዛም እግዚአብሔር የሙሴን ስም ጠራ፡፡ *ቀጥሎ ያለውን ክፍል ለመናገር የመጸሐፍ ቅዱስን ቃል ይጠቀሙ፡፡እግዚአብሔር በዚያ ስለነበር "የተቀደሰ መሬት" ማለት በጣም ልዩ ቦታ እንደሆነ አስረዱ፡፡ምክንያቱም ፡፡ እግዚአብሔር ቅዱስና ከእኛ የተለየ እንደሆነ ልንረዳ ይገባል፡፡ ከእኛ በተቃራኒ፣ እግዚአብሔር ኃጢአት የለበትም፡፡* ሙሴ ጫማውን አወለቀና ፊቱን ሸፈነ ምክንያቱም የእግዚአብሔርን ታላቅነት ተረድቷል፡፡ ***(ዘጸአት 3፡ 1 – 6)***<br>• *ለእግዚአብሔር ቅድስና ክብር ሊኖረን ይገባል፡፡ ለእስራኤላውያን በግብፅ ውስጥ ህይወት እንዴት እደነበረ ልጆቹ እዲያስታውሱ አድርጉ፡፡* እግዚአብሔር ለሙሴ እየተፈጠሩ የነበሩትን ሁሉንም መጥፎ ነገሮች እንደሚያውቅና አሁን ደግሞ ከግብፅ ውስጥ ወደ አዲስ ምድር ሊያወጣቸው እደነበር ነገረው፡፡እግዚአብሔር ሙሴ መሪያቸው እንዲሆንና ሄዶ ንጉስ ፈርኦንን እንዲያናግር ፈልጎ ነበር፡፡ *ወደ ፈርኦን ስለመመለሱ ሙሴ ምን ተሰምቶት ሊሆን እንደሚችል መርምሩ፡፡* ***(ዘጸአት 3 ፡ 7 – 10)***<br>• *ልጆቹ በመግቢያው ላይ የነበራቸውን የግል ምላሽ እና ሙሴ መሪ ሲሆን ስለተሰማው ስሜት የገመቱትን ማንኛውምን ትክክለኛ ግምት አገናኙ፡፡ ከዛም በመጸሐፍ ቅዱስ ንባቡ ላይ እንደተሰጠው እና በደረጃ 2 ትምህርት ላይ እንዳሉት የንግግር ስዕሎች የሙሴን ተቃውሞዎችና የእግዚአብሔርን ምላሾች አገናኙ፡፡*<br><br>• እኔ በቂ አይደለሁም - እኔ ከአንተ ጋር እሆናለው፡፡ ***(3፡ 11፣ 12)*** - ስምህን አላውቀውም - እኔ እኔ ነኝ (ይህ ስም እግዚአብሔር ሁሉን ቻይ መሆኑን ያሳያል) ፡፡ እኔ የአባቶችህ አምላክ ነኝ፣ የአብርሀም አምላክ ***(3፡ 13 – 15)*** አያምኑኝም - ሀይሌን እንድታረጋግጥ ተአምራቶችን ሰጥሀለው፡፡ ***(4፡ 1 – 9)*** ትክክለኛ ቃላቶችን መናገር አልችልም - እንድትናገር ረዳሀለው እና ምን ማለት እንዳለብህ አስተምርሀለው፡፡ ***(4፡ 10 – 12)*** እባክህ ሌላ ሰው ላክ፡፡ ***(4፡ 13)*** - አሮን ረዳትህ ይሆናልና ምን ማለት እንዳለበት ልትነግረው ትችላለክ፡፡<br>*ሙሴ መሪ ይሆናል ብለው የሚጠብቁት አይነት ሰው ነው? ባቀረባቸው ምክንያቶች እግዚአብሔር ደስ ያለው ይመስላችኋል? አይ!* ግብፅ ውስጥ የሰራው ስህተት እና ያቀረባቸው ምክንያቶች ቢኖሩም እንኳን የእግዚአብሔር ምርጫ ነበር፡፡ በቀጣዩ ታሪካችን ሙሴ በመጨረሻ እንዴት ለመታዘዝ ዝግጁ እንደሆነ እና እግዚአብሔር ፍቃዱን በህይወቱ ላይ መፈጸሙን መቀጠል መቻሉን እንማራለን፡፡ ወደፊት ለሚሆነው ነገር ሁሉ ሙሴ በእግዚአብሔር መታመን አለበት፡፡<br>• አንዳንዴ ከባድ የሚመስሉ ነገሮችን እንድናደርግልት እግዚአብሔር ይጠይቀናል፡፡ እርሱ ከእኛ ጋር እንደሆነና እንደሚረዳን ማስታወስ አለብን፡፡<br><br>**የመጽሐፍ ቅዱስ ጊዜ ትምህርቱን አጠናቁ፡፡**<br>**አሳዩ፡** FBI: ሙሴና የሚቃጠለው ቁጠቋጦ፡፡ |
| አስጠኑ | ቁልፍ ጥቅሱን አስፈላጊ በሆነበት ቦታ ላይ አስተምሩና አስረዱ፡፡ ***ዘጸአት 3፡ 12ሀ*** ከረዥም ታሪክ በኋላ ይሄ አጭር ጥቅስ ነው፡፡ ልጆቹ በግላቸው መፅሀፍ ላይ ምልክት ማድረግ ወይም በቡድን በመሆን እያንዳንዱ ልጅ ወረቀቶችን ያስጊጥና ደርድረው መስራት ወይም ትናንሽ ወረቀቶችን ፊደል ላይ ማጣበቅም ይችላሉ፡፡ |
| እዲታወስ | • ሙሴ ያየው ቁጥቋጦ የተለየ ነገሩ ምንድነው?<br>• በተቀደሰው መሬት ላይ እያለ ሙሴ ምን ነበር ያደረገው?<br>• ቅዱስ ምን ማለት ነው?<br>• እግዚአብሔር ሙሴ ምን ስራ እንዲሰራ ነበር የፈለገው?<br>• ሙሴ ስለራሱ ያቀረበውን ምክንያት ስጡ፡፡<br>• ሙሴ ስለእግዚአብር ምን ምክንያት አቅርቦ ነበር?<br>• እግዚአብሔር ለሙሴ የፈቀደለት አብሮት ማንን እንዲወስድ ነበር?<br>• እግዚአብሔር በሙሴ ተስፋ አልቆረጠም ነበር፡፡ ለምን? |

## ለ9 ታሪክ 4

**ሙሴ የእግዚአብሔርን መልዕክት አመጣ ፡ ይህ ታሪክ ስለ ሙሴ ወደ ግብፅ መመለስ ነው፡፡**

<table>
<tr><td></td><td>እየተማርን ያለነው፡<ul><li>ሙሴ እግዚአብሔር እንዲያደርግ ለጠየቀው ነገር በመጨረሻ ታዛዥ ሆነ፡፡</li><li>እግዚአብሔር የገባቸውን ተስፋዎች በመጠበቅ በሙሴ ህይወት ውስጥ ፍቃዱን ፈጸመ፡፡</li></ul>ቁልፍ ጥቅስ፡ ዘጸአት 4፡ 15<br>የመጽሐፍ ቅዱስ የንባብ ክፍል፡ ዘጸአት 4፡ 1-31</td></tr>
<tr><td>አስተዋውቁ</td><td>በህይወታችን ውስጥ ስላሉ አስፈላጊ ለውጦች አውሩ - ለምሳሌ፡-ቤት መቀየር፣ ወደ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት መግባት፣ ማግባት፡፡ ሙሴ በህይወቱ ብዙ ለውጦች ነበሩት - በልጅነቱ የመጀመሪያዎቹን ወራቶች አስታውሱ፣ ከዛም 40 አመቱ እስኪሆን ድረስ በፈርኦን ቤተመንግስት መኖር፣ ለሌላ 40 አመታት በበረሀ ውስጥ ኖረ፡፡ (በክፍል ውስጥ በሙሴ ህይወት የጊዜ መስመር መሰረት የእነዚህን ክስተቶች ምስሎች ብታስቀምጡ ጠቃሚ ነው፡፡) አሁን ሙሴ የህይወቱን ትልቅ ተግዳሮት እየገጠመ ነበር፡፡ እግዚአብሔር ምን እንዲያደርግ ጠይቆት ነበር?</td></tr>
<tr><td>አስተምሩ</td><td><ul><li>ሙሴ አሁን በምድያም ምድር አንድ ሚስትና ሁለት ልጆች ነበሩት፡፡ አማቹን፣ ዮቶርን፣ ወደ ግብፅ መመለስ ይችል እንደሆነ ጠየቀው፡፡ ዮቶር ተስማማ እና ሙሴ በአህያ ላይ ከሚነዱት ከሚስቱና ከልጆቹ ጋር ወጣ፡፡ ሙሴ እግዚአብሔር እንዲጠቀም ያዘዘውን ልዩ በትርም ይዞ ነበር፡፡ ለመጨረሻ ጊዜ በግብፅ እያለ ሊገድሉት የሚፈልጉት ሰዎች አሁን በህይወት እንደሌሉ እግዚአብሔር ለሙሴ ነገረው፡፡ ሙሴ እንዳይፈራ እግዚአብሔር እየረዳው ነበር፡፡ እግዚአብሔር ለሙሴ የገባውን ቃል መፈጸም ጀምሯል፡፡ ያለፈውን ሳምንት ቁልፍ ጥቅስ ማስታወስ ትችላላችሁ? (ዘጸአት 4፡ 18 – 20)</li><li>እግዚአብሔር ለሙሴ የገባለትን ሌላም ቃል ፈጸመ፡፡ ሙሴ ገና በመንገድ ላይ ሳለ ወንድሙ አሮን መጥቶ አገኘው፡፡ አሮን ለምን ነበር ከሙሴ ጋር ሊሆን የነበረው? ሙሴ እግዚአብሔር ያለውን ነገር ሁሉ፣ በበትሩ እንዲያደርግ የተሰጠውንም ምልክቶች ሳይቀር ለአሮን ነገረው፡፡ እግዚአብሔር ቃሉን እንደሚጠብቅ ሁልጊዜ በእርሱ መተማመን ይቻላል፡፡ የእርሱ ከሆንን ለእኛም እንደዛው ያደርግልናል፡፡ (ዘጸአት 4፡ 27፣ 28)</li><li>ሙሴና አሮን ግብፅ ሲደርሱ ከእስረራኤል መሪዎች ጋር ተገናኙና የእግዚአብሔርን እቅድ ነገሯቸው፡፡ ከዛም ሁሉም ሰዎች ተሰበሰቡና ሙሴ እግዚአብሔር በበትሩ እንዲያደርግ የሰጠውን ተአምራቶች አሳያቸው፡፡ ሙሴ በትሩን መሬት ላይ ሲወረውረው እባብ ሆነ ከዛ የእባቡን ጭራ ሲይዘው ድጋሚ በትር ሆነ፡፡ ቀጥሎ ካባው ውስጥ እጁን አስገባእና ሲያወጣው በለምፅ ተሸፍኖ ነበር (አሰረዱ) ነገር ግን ለሁለተኛ ጊዜ ሲያስገባው ተፈወሰ፡፡ (ዘጸአት 4፡ 6 - 9) ሰዎቹ እነዚህን ድንቅ ነገሮች ሲመለከቱ የእግዚአብሔርን ሀይል ማየት ይችሉ ነበር እና ሙሴ በትክክል ከእግዚአብሔር ዘንድ እንደተላከ ገባቸው፡፡ ሰዎቹ ምን የተሰማቸው ይመስላችኋል? (መደነቅ / እግዚአብሔር ከባርነት ሊያወጣቸው ስለነበር ደስታ) (ዘጸአት 4 ፡ 29 – 31)</li><li>ሙሴ ወደ ግብፅ ሲመለስ እግዚአብሔር መንገድ አዘጋጅቶለት በማየቱ ተደስቶ መሆን አለበት፡፡ በዚህ ታሪክ ውስጥ የእግዚአብሔር እቅድ ወደፊት እንዲሄድ ያደረጉትን ሰዎች ተመልከቱ - ዮቶር፣ አሮን፣ መሪዎቹና ህዝቡ፡፡ ሙሴ እና አሮን አሁንም እቅዱን ለማን ማቅረብ ነበረባቸው? ምንም ቀላል ባይሆንም እንኳን፣ ነገሮችን እንዲሰራ አሁንም በእግዚአብሔር መደገፍ እንደሚችሉ እጸትን ስጡ፡፡ እሱ እየተቆጣጠረ ነበር!</li></ul>የመጽሐፍ ቅዱስ ጊዜ ትምህርቱን አጠናቁ፡፡<br>አሳዩ፡ FBI: ሙሴና የሚቃጠለው ቁጥቋጦ - ገፅ 21-24</td></tr>
<tr><td>አስጠኑ</td><td>ቁልፍ ጥቅሱን አስፈላጊ በሆነበት ቦታ ላይ አስተምሩና አስረዱ፡፡ ዘጸአት 4፡ 15 ሙሴና አሮን አንድ ላይ መስራታቸውና እግዚአብሔር ከእነሱ ጋር መሆኑ ጋር የተያያዘው በዚህ ጥቅስ ዙሪያ ያለው ሀሳብ ልጆቹ እንደገባቸው አረጋግጡ፡፡</td></tr>
<tr><td>እዲታወስ</td><td>የቀደሙት ታሪኮችን ጥያቄዎች እና ለታሪክ 4 ቀጥሎ ያሉትን ጥያቄዎች በመጠቀም እስካሁን ያለውን የሙሴን ህይወት ከልሱ፡<ul><li>ማን ነበር ከሙሴ ጋር ወደ ግብፅ የተመለሰው?</li><li>በመንገድ ላይ ማን አገኘው?</li><li>ሙሴ በእግዚአብሔር እንደታላከ ህዝቡ እንዴ አወቀ?</li><li>ሙሴ በህዝቡ ፊት ያደረገውን አንዱን ተአምራት አስረዱ፡፡</li></ul></td></tr>
</table>

<u>**ለ10 ታሪክ 1**</u>

**ሙሴና የመጀመሪው መቅሰፍት - ይህ ታሪክ እግዚአብሔርን ስለመታዘዝ ነው።**

**እየተማርን ያለነው:**

- የእግዚአብሔር ትዕዛዛት ሊደመጡና ሊደረጉ ይገባል።
- እግዚአብሔርን ለመስማት እና ለመታዘዝ እንቢ ማለት ሁሌም መጨረሻው ቅጣት ነው።

**ቁልፍ ጥቅስ:** ***ዘጸአት 7፡ 16***

**የመጽሐፍ ቅዱስ የንባብ ክፍል:** ***ዘጸአት 7፡ 1-24***

### አስተዋውቁ

መታዘዝ ስላለብን ህጎችና ስለአለመታዘዝ ውጤቶች ከልጆቹ ጋር አውሩ፣ በትምህርት ቤት ውስጥ ወይም ሰፋ ባለ ማህበረሰብ ውስጥ ሊሆን ይችላል። ከዛሬው ክፍል ጋር ለማገናኘት ለ9 ታሪክ 4ን ከአንዳንድ ጥያቄዎችን ጋር ማየት ጠቃሚ ሊሆን ይችላል።

### አስተምሩ

- አሁን ሙሴና ፈርኦን እስራኤላውያን ግብፅን ለቀው በምድረበዳ እግዚአብሔርን እንዲያመልኩ ፈርኦንን የሚጠይቁበት ጊዜ ደርሶ ነበር። *ምላሹን እንዲገምቱ ልጆቹን ጠይቁ። እንቢ ማለቱንና ነገሮችን ከበፊት ይልቅ ስላባባሰው ውጤት አስረዱ። ፈርኦን ለእግዚአብሔር እየታዘዘ እንዳልሆነ ልጆቹ እንዲያዩ እርዷቸው። እስራኤላዊ ብትሆኑ ኖሮ ስለ ሙሴ ምን ታስቡ ነበር?* ***(ዘጸአት 5፡ 1 – 21)***

  እግዚአብሔር ይህ እንዲፈጠር ለምን እንደፈቀደ ሙሴ ሊገባው አልቻለም ነበር። ስለ ጉዳዩ እግዚአብሔርን ጠየቀ። ታላቅ ሀይሉን እንደሚያሳይ እግዚአብሔር ቃል ገባላቸው፤ ፈርኦን በመጀመሪያው ባይታዘዝም እንኳን በመጨረሻ ግን እግዚአብሔር የጠየቀውን እንዲፈፅም ያደርገው ነበር። *እኛ ቃል እንገባለን እና እንረሳለን ወይም አናደርገውም ነገር ግን የእግዚአብሔር ቃል ሁሌም እንደሚፈጸም ልጆቹን አስታውሷቸው።*
- እግዚአብሔር በድጋሚ ወደ ፈርኦን እንዲሄዱና እስራኤላዊ ባሪያዎችን እንዲለቅ እንዲጠይቁ ነገራቸው! **(ዘጸአት 5፡ 22 – 7፡5)**
- በዚህ ጊዜ ፈርኦን ተአምራት እንዲያደርጉ ጠየቀና የአሮን በትር እባብ ሆነ። የፈርኦን አስማተኞችም ተመሳሳይ ነገር አደረጉ ግን የአሮን እባብ የአስማተኞቹን እባብ ሁሉ ዋጠ። *ይህ ስለ እግዚአብሔር ምን አሳየ?* አሁንም ፈርኦን ለእግዚአብሔር አልታዘዘም። ***(ዘጸአት 7፡ 6-12)***
- ከዛም እግዚአብሔር ሙሴ እና አሮን ፈርኦንን አባይ ወንዝ ጋር እንዲያገኙት ነገራቸው። የእግዚአብሔር ተዕዛዝ በድጋሚ ተሰጠ። ፈርኦን የማይታዘዝ ከሆነ አባይ ወንዝ ወደ ደም ይቀየራል እና ምንም አይነት ንፁህ ውሀ አይኖርም እና ሁሉም አሳዎች ይሞታሉ። ፈርኦን ለመስማት እንቢ አለ። ዞሮ ወደ ቤቱ እንደሄደ መፅሀፍ ቅዱስ ይናገራል። የፈርኦንን አኳኋን ተወያዩ - ምን ቃላት ይገልፁታል? መጽሐፍ ቅዱስ ደንዳና ልብ እንዳለው እንደሚገልፅ አስረዱ። ***(ዘጸአት 7፡ 14-19)***
- ስለዚህ ሁሉም ግብፃውያን የሚጠጣ ውሀ ለማግኘት የወንዙን ዙሪያ ሁሉ ቆፈሩ፣ ምክንያቱም የወንዙን ውሀ መጠጣት አልቻሉም። ይህ የመጀመሪያው መቅሰፍት ነበር እና ለ7 ቀናት ነው የቆየው። ***(ዘጸአት 7፡ 24-25)***

- *ሙሴና አሮን ልክ እግዚአብሔር እንዳላቸው ነበር ያደረጉት፣ እያንዳንዱን ነገር በመታዘዝ። ይሄንን ነው ሁሌም መጣርና ማድረግ ያለብን። በእኛ መታዘዝ እግዚአብሔር እንደሚደሰት መጽሐፍቅዱስ ይናገራል! ፈርኦን እግዚአብሔርን አልታዘዘምና ለመስማትም አልፈለገም ነበር እና ይህ ደግሞ መጨረሻው ሁሌም ችግርና የእግዚአብሔር ቅጣት ነው።ቀን በቀን ህይወታችን እንድናደርጋቸው እግዚአብሔር ስላዘዘን አይነት ነገሮች ተወያዩ።*

**የመጽሐፍ ቅዱስ ጊዜ ትምህርቱን አጠናቁ።**

**አሳዩ:** FBI - ሙሴ ወደ ፈርኦን ሄደ፣ ሙሴና መቅሰፍቶቹ ክፍል 1

### አስጠኑ

ቁልፍ ጥቅሱን አስፈላጊ በሆነበት ቦታ ላይ አስተምሩና አስረዱ - ***ዘጸአት 7፡ 16***

### እዲታወስ

ታሪኩን ለመከለስ እንዲረዳ ልጆቹን ቀጥሎ ያሉትን ጥያቄዎች ጠይቋቸው።.

- እግዚአብሔር ለሙሴና ለአሮን ቃል የገባላቸው ነገር ምን ነበር?
- አሮን ያደረገው የመጀመሪያው ተአምራት ምን ነበር?
- በመጀመሪያው መቅሰፍት አባይ ወንዝ ላይ ምን ተፈጠረ?
- ግብፃውያኑ ለሰባት ቀን ያልነበራቸው ነገር ምን ነበር?
- እግዚአብሔር በቀን ለቀን ህይወታችን ምን አይነት ነገሮችን እንድናደርግ አዞናል?

## ለ10 ታሪክ 2

**ሙሴና የመጨረሻው መቅሰፍት - ይህ ታሪክ ዕብራውያኖችን ለማዳን የእግዚአብሔርን እቅድ የሚያሳይ ነው፡፡**

**እየተማርን ያለነው፡**

- ፈርኦን እና ግብፃውያኑ እግዚአብሔርን አለመታዘዛቸው መቀጣት አለበት፡፡
- እግዚአብሔር ኃጢአትን ችላ ማለት አይችልም ነገር ግን የመዳንን መንገድ ያዘጋጃል፡፡

**ቁልፍ ጥቅስ፡ *ዘጸአት 12፡ 13***

**የመጽሐፍ ቅዱስ የንባብ ክፍል፡ *ዘጸአት 11፡ 1-10፣ 12፡ 1-13***

### አስተዋውቁ

በአንዳንድ ሁኔታዎች እንዴት እንደምንጠበቅ ተወያዩ፡፡ ልጆች ሊያውቁት የሚችሉትን ምሳሌ ምረጡ ለምሳሌ፡- ከጸሀይ የሚከላከል ክሬም መቀባት ነጣ ያለ ቆዳ ያላቸውን ሰዎች ጸሀይ ከሚያደርሰው ጉዳት ይጠብቃል፡፡ ፓስፖርት መያዝ ከአንድ ሀገር ወደሌላ ሀገር ማለፍ እንዲቻል ያደርጋል፡፡ ክትባት በሽታ እንዳይዘን ይከላከላል፡፡ በዛሬው ታሪክ እግዚአብሔር ከቅጣት መጠበቃቸውን ለማረጋገጥ እንዴት ለእስራኤላውያን ልዩ ምልክት እንደሰጣቸው እንማራለን፡፡

### አስተምሩ

- እስካሁን ድረስ ዘጠኝ መቅሰፍቶች ሆነዋል ግን በእያንዳንዱ ጊዜ ፈርኦን ሊለቃቸው ፈቃደኛ አልነበረም፡፡ እግዚአብርሄር እንዴት ትልቅ እንደሆነ እስኪያስተውል ድረስ እግዚአብሔር የፈርኦንን ልብ እያደነደነ ነበር፡፡

- አሁን ፈርኦን እንደገና ሊያየው እንደማይፈልግ ለሙሴ ነግሮት ነበር፡፡ ***(ዘጸአት 10፡ 27-29)*** ነገር ግን እግዚአብሔር የመጨረሻው መቅሰፍት ምን እንደሚሆን ለሙሴ አስረድቶት ነበር፡፡ ሁሉም ቤተሰብ ላይ ከባድ ቅጣት ሊሆን ነበር፤ ከሁሉም ቤተሰብ የመጀመሪያ ወንድ ልጅ ሊሞት ነበር፡፡ ***(ዘጸአት 11፡ 4-6)*** ነገር ግን ፈርኦን እግዚአብሔር ይሄን ከባድ ቅጣት ሊያመጣ ይችላል ወይም ያመጣል ብሎ አላመነም ነበር፡፡ ***(ዘጸአት 11፡ 10)***

- *እግዚአብሔር በመጽሐፍ ቅዱስ የሚለው ወይም የሚናገረው ማንኛውም ነገር እውነት እንደሆነ መማር አለብን፣ እና ቃል የሚገባውን ማንኛውንም ነገር ያደርገዋል፡፡*

- ከዘያም ጌታ እስራኤላውያን ግብፅን ለመልቀቅ ማድረግ ያለባቸውን ዝግጅት ለሙሴ አስረዳው፡፡ እያንዳንዱ ቤተሰብ አንድ ጠቦት ማረድ ነበረበት፡፡ ቤቱ የእስራኤላዊያን እንደሆነ የሚያሳይ ጥቂት ደም በቤቱ በር ዙሪያ ላይ ሊቀባ ነበር፡፡ ከዛም ልዩ የሆነ የተጠበሰ ጠቦት፣ የዳቦ እና የመራራ ቅጠል ምግብ ሊበሉ ነበር፡፡ ምግቡን በፍጥነት ሊበሉትና በጣም በቅርቡ ለመሄድ ለባብሰው ሊዘጋጁ ነበር፡፡ በግብፃውያን ቤቶች ውስጥ የመጀመሪያ ወንዶች ልጆች በተገደሉ ጊዜ እስራኤላውያን በበራቸው ላይ ደም ካለ ደህና እንደሚሆኑ ጌታ አስረዳቸው፡፡
***(ዘጸአት 12፡ 12-13)*** *በመጨረሻም ሊወጡ ስለነበር የነበረውን ጉጉት እና አጠባበቅ እና እስራኤላውያን ልክ እንደታዘዙት እንዴት እንዳደረጉ ግለፁ፡፡ ለእስራኤላውያን የደሙን ዋጋ እና ጥቅም እና ያላቸው ብቸኛ ጥበቃ እንደነበር አብራሩ፡፡*

- *እግዚአብሔር የሚሰራበትን መንገዶች መረዳት ለእኛ ሁሌም ቀላል አይደለም፣ ነገር ግን ሁሌም ቢሆን የተሻለውን እንደሚያውቅ እርግጠኛ መሆን እንችላለን፡፡ እስራኤላውያን እንዴት ነበር የተጠበቁት? በተመሳሳይ መንገድ ጌታ ኢየሱስ መስቀል ላይ እንደሞተ የሚያምን ማንኛውም ሰው በኃጢአታችን ምክንያት ከሚመጣብን ቅጣት ይድናል፡፡ ጌታ ኢየሱስ የእግዚአብሔር በግ እንደሆነ መጽሐፍቅዱስ ያስረዳናል፣ ለእስራኤላውያን ብቻ ሳይሆን ግን እኛንም ጨምሮ ለመላው አለም ነው፡፡ በመስቀል ላይ ሲሞት በፈሰሰልን ደሙ ስናምን፣ ለኃጢአታችን ከሆነው ቅጣት እንድናለን፡፡*

**የመጽሐፍ ቅዱስ ጊዜ ትምህርቱን አጠናቁ፡፡**
**አሳዩ፡** FBI- ሙሴ እና መቅሰፍቶቹ ክፍል 2

### አስጠኑ

ቁልፍ ጥቅሱን አስፈላጊ በሆነበት ቦታ ላይ አስተምሩና አስረዱ - ***ዘጸአት 12፡ 13***

### እዲታወስ

ታሪኩን ለመከለስ እንዲረዳ ልጆቹን ቀጥሎ ያሉትን ጥያቄዎች ጠይቋቸው፡፡.

- ለእግዚአብሔር ቅጣት ልንጠቀመው የምንችለው ሌላ ቃል ምንድን ነው?
- ለፈርኦን የመጨረሻው ቅጣት ምን ሊሆን ነበር?
- ደህና መሆናቸውን ለማረጋገጥ እስራኤላውያን ምን ማድረግ ነበረባቸው?
- ምን መብላት እና እንዴት መብላት ነበረባቸው?
- ጌታ ኢየሱስ መዳን እንድንችል ያደረገው እንዴት ነው? ***(ሮሜ 5፡ 8)***

# <u>ለ10 ታሪክ 3</u>

**ሙሴና ከግብፅ መውጣት - ይህ ታሪክ ስለ እግዚአብሔር ድንቅ ሀይል ነው፡፡**

**እየተማርን ያለነው፡**

- እግዚአብሔር የሚቃጠለው ቁጥቋጦ ጋር ሙሴን ሲያናግረው ቃል እንደገባው እስራኤላውያንን ነፃ አወጣቸው፡፡
- መጽሐፍ ቅዱስ ብዙ ጊዜ ይሄንን ክስተት የእግዚአብሔር ሀይል ከሚባሉት ታላላቅ ምሳሌዎች ውስጥ አንዱ እንደሆነ ይናገራል፡፡

**ቁልፍ ጥቅስ፡ *ዘጸአት 14፡ 30***

**የመጽሐፍ ቅዱስ የንባብ ክፍል፡ *ዘጸአት 12፡ 31-39፣ 14፡ 1-31***

## አስተዋውቁ

እኛ ማድረግ የማንችላቸውን አንዳንድ ነገሮች አስቡ፡፡ ያለ አውሮፕላን መብረር፣ ያለ ጀልባ ባህር መሻገር፣ ያለ ኮምፓስ በበረሀ ውስጥ መንገዳችንን መፈለግ ወዘተ. ቢሆንም ግን ለሰው የማይቻል ለእግዚአብሔር ይቻላል፡፡ በዚህ ታሪክ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ከተመዘገቡት ከሀይሉ እጅግ በጣም ታላላቅ ማሳያዎች አንዱን ሊያሳይ ነበር፡፡

## አስተምሩ

- በሌሊት፣ የግብፃውያን የመጀመሪያ ወንድ ልጆች ሲሞቱ፣ ፈርኦን ሙሴንና አሮንን አስጠራ፡፡ ከዚህ በፊት ከነበሩት መቅሰፍቶች ሁሉ በኋላ ፈርኦን ምን አይነት ምላሽ ሰጠ? *ይሄ ጊዜ እንዴት ይላይ እንደነበር አስረዱ* - ሁሉንም ሰዎች ከመንጎቻቸር ጋር እንዲወስዱ እና በአንድ ጊዜ ግብፅን ለቀው እንዲወጡ ነገራቸው፡፡ ***(ዘጸአት 12፡ 31-32)*** ግብፃውያኑም እንዲሄዱ አበረታቷቸው ምክንያቱም እስራኤላውያን ከቆዩ ሁሉም ይሞታሉ ብለው ፈርተው ነበር፡፡ ሲሄዱ ግብፃውያኑ የብር፣ የወርቅና የልብስ ስጦታዎችን እንዲሰጡ ጌታ አነሳሳቸው፡፡ ***(ዘጸአት 12፡ 35-36)*** ባጠቃላይ ከስድስት መቶ ሺህ በላይ ወንዶች፣ እንዲያውም ሴቶችና ህፃናት ነበሩ፡፡ *ተለቅ ካሉ ህፃናት ጋር ይህንን ቁጥር ተመሳሳይ የህዝብ ቁጥር ካለው ቦታ ጋር ማነፃጸር ትችላላችሁ፡፡*
- በመጨረሻ ፈርኦን ለእግዚአብሔር እየታዘዘ ነበር! መጀመሪያ ይህን ቢያደርግ ብዙ ስቃይን ማስቀረት ይችል ነበር፡፡ *በድጋሚ ለወላጆች፣ ለአስተማሪዎች እና ከሁሉም በላይ ለእግዚአብሔር የመታዘዝን አስፈላጊነት አፅንኦት ይስጡ!*
- እስራኤላውያን በሙሴ እየተመሩ ወደ ቀይ ባህር ተጓዙ፡፡ *ስሜታቸውን መርምሩ፡፡* ነገር ግን የፈርኦንን ነገር ሲያዩ የመጨረሻቸው አልነበረም! እግዚአብሔር ምንኛ ታላቅ አምላክ እንደሆነ ገና መማር ስለነበረበት በድጋሚ እግዚአብሔር የፈርኦንን ልብ አደነደነ! ፈርኦን አናፂዎቹን ሁሉ ማጣቱን በድንገት አስተዋለ እና በ600 ሰረገላዎች ሊያሳድዳቸው ወሰነ፡፡ ***(ዘጸአት 14፡ 3-7)***
- እስራኤላውያን ወጥመድ ውስጥ ነበሩ! ፈርኦን ከኋላቸው ነበር እና ቀይ ባህር ደግሞ ከፊታቸው፡፡ *አሁን ምን የተሰማቸው ይመስላቹሀል? ድንጋጤያቸውንና ሙሴን እንዴት እንደከሰሱት ግለፁ፡፡* ሙሴ ጠንክረው እንዲቆሙ እና ጌታ ወደእነሱ የሚያመጣውን ማዳን እንደሚያዩ ነገራቸው! ***(ዘጸአት 14፡ 10-14)***
- ጌታ በትሩን በባህሩ ላይ እንዲያነሳ ለሙሴ ነገረው፡፡ ሙሴ ሲታዘዝ፣ ሁሉም እስራኤላዊ በደረቅ ምድር እንዲሻገሩ በቀይ ባህር መካከል በተአምር ደረቅ መንገድ ተገለጠ፡፡
- *ግብፃውያን ሊከተሏቸው ሲሞክሩ ምን እንደተፈጠረ አስረዱ፡፡* ሙሴ በድጋሚ በትሩን አነሳ እና ውሀው ተመለሰ፡፡ የፈርኦን የጦር ሰራዊት በጠቅላላ በውሀው እንደተሸፈኑና አንዳቸውም እንዳልተረፉ መፅሀፍ ቅዱስ ይናገራል፡፡ ***(ዘጸአት 14፡ 28)*** *እስራኤላዊ ብትሆኑ ኖሮ ስለእግዚአብሔር ምን ታስቡ ነበር? ለእግዚአብሔር ታላቅ ሀይል ምላሻቸውን ግለፁ - እግዚአብሔርን ይፈሩ እንደነበር(አስረዱ) እና በእርሱና በሙሴ የነበራቸውን እምነት አስቀምጡ፡፡* ***(ዘጸአት 14፡ 31)***
- በታላቅ ሀይሉ ምክንያት ሁልጊዜ ጌታን መታመን እንደምንችል መማር እንችላለን፡፡ እንደ እስራኤላውያ እርሱን ማመን እና "ጌታ ሆይ አድነኝ!" ማለት አለብን፡፡

**የመጽሐፍ ቅዱስ ጊዜ ትምህርቱን አጠናቁ፡፡**
**አሳዩ፡** FBI- ሙሴ እና መቅሰፍቶቹ ክፍል 2፣ እና ሙሴ፡ ቀይ ባህር መሻገር

## አስጠኑ

ቁልፍ ጥቅሱን አስፈላጊ በሆነበት ቦታ ላይ አስተምሩና አስረዱ - ***ዘጸአት 14፡ 30***

## እዲታወስ

ታሪኩን ለመከለስ እንዲረዳ ልጆቹን ቀጥሎ ያሉትን ጥያቄዎች ጠይቋቸው፡፡.

- ፈርኦን ለምን ነበር እስራኤላውያንን ለመልቀቅ የወሰነው?
- ግብፃውያኑ ምን ነበር የሰጧቸው?
- ፈርኦን ለምን ነበር እነሱን ለማሳደድ የወሰነው?
- እስራኤላውያን ለምን ነበር የደነገጡት?
- እግዚአብሔር የሚያድናቸውን ምን እንዲያደርግ ለሙሴ የነገረው?
- የግብፅ የጦር ሰራዊት ምን ሆነ?
- እስራኤላውያን የሆነውን ነገር ባዩ ጊዜ ምን አደረጉ?

## <u>ለ10 ታሪክ 4</u>

**ሙሴና እስራኤል እግዚአብሔርን አመሰገኑ - ይህ ታሪክ እግዚአብሔርን ስለማመስገን ነው፡፡**

| | |
|---|---|
| | **እየተማርን ያለነው፡**<br>• እስራኤላውያን እግዚአብሔር ነፃነትና ጥበቃ ሊሰጣቸው ስላደረገው ነገር ሁሉ አመስጋኞች ነበሩ፡፡<br>• ሁላችንም አቁመን ፣ ወደኋላ መመልከትና በህይወታችን ውስጥ ስላደገው ነገር እግዚአብሔርን ማመስገን አለብን፡፡<br><br>**ቁልፍ ጥቅስ፡ *መዝሙረ ዳዊት 106፡1***<br>**የመጽሐፍ ቅዱስ የንባብ ክፍል፡ *ዘጸአት 15፡ 1-22*** |
| አስተዋውቁ | በመፅሀፍ ቅዱስ ዘመን የተከናወኑ አንዳንድ አስደናቂ ነገሮችን ለማስታወስ ፍንጮችን ተጠቀሙ፡፡ ለምሳሌ፡- ዳንኤል በአንበሶች ጉድጓድ ውስጥ መዳኑ፣ ዳዊት ጎሊያድን ሲገድል ወዘተ፣ ባለፈው ሳምንት ታሪክ ውስጥ እንደነበረው ቀይ ባህርን መሻገርንም ያጠቃልላል፡፡ ካላችሁ፣ በመፅሀፍ ቅዱስ የጊዜ ሰሌዳ ላይ ክስተቶችን አስቀምጡ፡፡ እነዚህ እያንዳንዳቸው የመጽሐፍ ቅዱስ ገጸ-ባህሪያቶች በእግዚአብሔር ታላቅ ሀይል ከመደገፍ በስተቀር ምንም ምርጫ አልነበራቸውም፡፡ እግዚአብሔር ካዳናቸው በኋላ እስራኤላውያን ምን እንዳደረጉ እናያለን እና በተጨማሪም ለእኛ ስላደረገልን ነገር ለእግዚአብሔር እንዴት ምላሽ መስጠት እንዳለብን አስቡ፡፡ |
| አስተምሩ | • እስራኤላውያን በመጨረሻ ከባርነት ነፃ ወጥተው ነበር እና ጠላቶቻቸው በሙሉ ሰምጠዋል፡፡ *ምን ተሰምቷቸው ሊሆን እንደሚችል አብራሩ፡፡* እግዚአብሔር እንደሆነ ያዳናቸው አውቀው ነበር እናም ስላደረገው ነገር በምስጋና ስለተሞሉ እግዚአብሔርን ማክበር ፈለጉ፡፡ ***(ዘጸአት 15፡ 1)*** እግዚአብሔር ታላቅ መሆኑን አስተውለው ስለ ክብሩ ዘመሩ ምክንያቱም እንደዚህ አይነት ሀይል ያለው ሌላ እግዚአብሔር እንደሌለ አውቀዋል፡፡ ***(ዘፍጥረት 15፡ 11)*** ለእነሱ ስላደረገው ነገር ሁሉ በዝርዝር ዘመሩ፡፡<br>• *እግዚአብሔር እንዴት ትልቅ እንደሆነ እና ይሄን እንዴት በዙሪያች ባሉት ፍጥረታት ውስጥ ሁሉ ፣በእያንዳንዱ ቀን የሚያስፈልጉንን ነገሮች ሁሉ ማቅረቡንና በተጨማሪም ለእኛ ብሎ በመስቀል ላይ እንዲሞት ልጁን በመላኩ ፍቅሩን እንደምናይ ልጆቹ ማስተዋል አለባቸው፡፡*<br>• እስራኤላውያን ስለእግዚአብሔር ብቻ አልነበረም የዘመሩት፣ ከእርሱ ጋር የጠበቀ ግንኙነት ነበራቸው ስለሆነም "አምላኬ"፣ "ብርታቴ"፣ "አዳኜ" ብለው ጠሩት፡፡ ***(ዘጸአት 15፡ 2)***<br>• *ልጆቹ ስለእግዚአብሔር ብቻ ወይም ጌታን እንደየግል አዳኛቸው ያውቁት እንደሆነ ሊጠየቁ ይችላሉ፡፡*<br>• እስራኤላውያን አሁን ስላለው ብቻ አላሰቡም፣ ወደ ተስፋይቱ ምድር በሚጓዙበት ወቅት ከሌሎች ጠላቶች ጋር በሚደረጉ የወደፊት ጦርነቶች ላይ እርሱን ማመን እንደሚችሉ ያውቁ ነበር፡፡ ጌታ መቼም እንደማይለወጥ እና ዛሬ ብቻ ሳይሆን ወደፊትም ሁሌ እርሱን ማመን እንደምንችል መማር እንችላለን፡፡<br>• የአሮን እህት ማርያም በዝማሬና በጭፈራ አንዳንድ ሴቶችን እየመራች ነበር፡፡ እግዚአብሔር ያደረገውን ነገር ሲያስታውሱ በጣም ተደስተው ነበር፡፡<br><br>**የመጽሐፍ ቅዱስ ጊዜ ትምህርቱን አጠናቁ፡፡**<br>**አሳዩ፡** FBI- ሙሴ፡ ቀይ ባህር መሻገር |
| አስጠኑ | ቁልፍ ጥቅሱን አስፈላጊ በሆነበት ቦታ ላይ አስተምሩና አስረዱ - ***መዝሙር 106፡ 1-*** ይህ ጥቅስ እግዚአብሔርን ስለማመስገን ያስታውሰናል ስለዚህ ልጆቹ ጌታ ስላደረገላቸው ነገር የምስጋና ጸሎት እንዲያዘጋጁ ይበረታታሉ፡፡ |
| እዲታወስ | ታሪኩን ለመከለስ እንዲረዳ ልጆቹን ቀጥሎ ያሉትን ጥያቄዎች ጠይቋቸው ወይም ለ10 ላይ በሙሉ በመመስረት ጥያቄዎችን ጠይቁ፡፡<br>ነፃ መሆናቸውን ሲያዩ እስራኤላውያን ምን ነበር ያደረጉት?<br>በመዝሙራቸው ውስጥ ጌታን እንዴት ነበር የገለፁት?<br>አስራኤላውያን ለወደፊት እግዚአብሔርን ማመናቸውን በምን ታውቃላችሁ?<br>ሴቶቹን በዝማሬ እና በጭፈራ ማን ነበር የመራው?<br>እስራኤላውያን ከመፍራትና ከመደንገጥ ወደ መዘመርና ማወደስ የተቀየሩት ለምን ይመስላቹሃል? |

## <u>ለ11 ታሪክ 1</u>
**እግዚአብሔር ምግብ ሰጠ - ይህ ታሪክ እግዚአብሔር ለእስራኤላውያን ምግብ ስለማዘጋጀቱ ነው።**

| | |
|---|---|
| | **እየተማርን ያለነው፡**<br>• እግዚአብሔር ለእስራኤላውያን ለአርባ አመታት በምድረበዳ ምግብ ሰጣቸው።<br>• ጌታ ኢየሱስ "የህይወት እንጀራ" ነው እናም ፍላጎታችንን ያሟላልናል።<br><br>**ቁልፍ ጥቅስ፡ *ዮሐንስ 6፡35***<br>**የመጽሐፍ ቅዱስ የንባብ ክፍል፡ *ዘጸአት 16፡ 1 – 32*** |
| አስተዋውቁ | ለ9 እና ለ10 ላይ ምን እንደተፈጠረ ልጆቹን በአጭሩ አስታውሷቸው። እስራኤላውያንን ከግብፅ በማውጣት እግዚአብሔር ለእነሱ ሀይሉን አሳይቷል እና አሁን ወደ አዲስ ምድር እንደሚመራቸው ቃል ገብቷል። ሩቅ ሳይሄዱ፣ ህዝቡ ስለመራባቸው ለሙሴ ማጉረምረምና ማማረር ጀመሩ! የያዙት ምግብ አልቋል እና ወደ ግብፅ ለመመለስና እዛ ስለበሉት ምግብ እያሰቡ ነበር። ***(ዘጸአት 16፡ 2-3)*** እግዚአብሔር እየተቆጣጠረ እንደሆነ እና ለጉዞ የሚያስፈልጋቸውን ነገር ሁሉ እንደሚያውቅ ረስተው ነበር። *ከተቻለ ይህ የተሳሳተ አመለካከት እንደሆነ ልጆቹን ማሳሰብ ትችላላችሁ። እግዚአብሔር አመስጋኞች እንድንሆን ይፈልጋል።* |
| አስተምሩ | • ምንም እንኳን ህዝቡ እግዚአብሔርን ባያምኑም፣ እርሱ ግን አሁንም ለእነሱ እንደሚያስብ አሳያቸው። ሁሌም ምግብ እንዲኖራቸው ለማድረግ እቅድ ነበረው። እንጀራ ከሰማይ ይልክና ሁሌ ጠዋት ጠዋት ይሰበስቡት ነበር። በሳምንቱ በስድስተኛው ቀን፣ ለሰንበት ቀን (የእግዚአብሔር ልዩ ቀን) እንዲያቆያቸው እጥፍ ይሰበስባሉ። በእያንዳንዱ ምሽት ስጋ ይቀበላሉ። ***(ዘጸአት 16፡ 4 – 12)***<br>• *ጠዋት ላይ እስራኤላውያን ከድንኳኖቻቸው ሲወጡ አስቡ እና ላገኙት ነገር ምላሻቸውን ግለፁ። ይህ ጌታ የሰጣቸው እንጀራ እንደሆነ ሙሴ አስረዳቸው። ሁሉም በድንኳኖቻቸው ለሚኖሩ ሰዎች በቂ መሰብሰብ ነበረባቸው። ማንም ለቀጣዩ ቀን ምንም ማስቀመጥ የለበትም ነበር። ቢሆንም ግን አንዳንድ ሰዎች ለማስቀመጥ ሞክረው ነበር ግን በቀጣዩ ቀን ተበላሸ።* ***(ዘጸአት 16፡ 15 - 20)*** *የራሳችንን ነገር ከማድረግ ይልቅ እግዚአብሔር ያዘዘንን ራሱን የማድረግን አስፈላጊነት ጥቀሱ።*<br>• ከሰማይ የወረደውን እንጀራ ህዝቡ "መና" አለው። ጣዕሙ እንደ ማር ነበር! እግዚአብሔር ጉዞአቸው እስኪጠናቀቅ ድረስ መናን ለእስራኤላውያን ላከ። እግዚአብሔር እርሱ አምላካቸው እንደሆነና እንደሚንከባከባቸው ተጨማሪ ማስረጃ ሰጣቸው። ***(ዘጸአት 16፡ 31)***<br>• በታሪካችን ውስጥ፣ እስራኤላውያን ረሀባቸውን ከማርካቱ በፊት መናውን መሰብሰብና መብላት ነበረባቸው። በምድረበዳ በእያንዳንዱ ቀን በህይወት ያቆያቸዋል ነገር ግን ሁሌም ተጨማሪ መና ይፈልጉ ነበር። በመጨረሻ ሞቱ።<br><br>• *ከብዙ አመታት በኋላ፣ ለኃጢአታችን ለመሞት ኢየሱስ ከሰማይ ወረደ። እራሱን "የህይወት እንጀራ" ብሎ ጠራ። ጌታ ኢየሱስን (የህይወት እንጀራ) ወደ ህይወታችን ከተቀበልነው የዘላለም ህይወት ይሰጠናል - እዚህ የምንደሰትበት ህይወት እናም ደግሞ በሰማይም። ከሰማይ የወረደው መና ለእስራኤላውያን ድንቅ ተአምራት ነበር ነገር ግን ጌታ ኢየሱስን በመቀበል ከዚህ በጣም የላቀ ነገር ሊኖረን ይችላል። ( ስለ መና እና ስለህይወት እንጀራ መረጃን በሁለት ሰሌዳዎች ወይም ሰንጠረዥ በማስቀመጥ ይህንን ትምህርት የበለጠ ግልፅ ለማድረግ ይፈልጉ ይሆናል።)*<br><br>**የመጽሐፍ ቅዱስ ጊዜ ትምህርቱን አጠናቁ።**<br>**አሳዩ፡** FBI ሙሴ እና እግዚአብሔር እንዴት በረሀ ውስጥ ምግብ እንዳዘጋጀ። |
| አስጡኑ | ቁልፍ ጥቅሱን አስፈላጊ በሆነበት ቦታ ላይ አስተምሩና አስረዱ። ***ዮሀንስ 6፡ 35*** ከላይ የተጠቀሰውን አጉሉ። |
| እዲታወስ | እዚህን ጥያቄዎች ፈተና ውስጥ ተጠቀሟቸው።<br>• ህዝቡ ለምን አጉመረመ?<br>• ለማን ነበር ያጉረመረሙት?<br>• በማጉረምረም ፋንታ ምን ማድረግ ነበረባቸው?<br>• በእያንዳንዱ ሳምንት ምን ያህል ቀን ነበር መና መሬት ላይ የሚገኘው?<br>• በእያንዳንዱ ምሽት ምን ነበር ያገኙት?<br>• ለምን ያህል ጊዜ ነበር መና የሰበሰቡት?<br>• ኢየሱስ ለራሱ ምን ስም ነበር የተጠቀመው?<br>• በምን መንገድ ነው ኢየሱስ ከመና በላይ የሆነው? |

## <u>ለ11 ታሪክ 2</u>

**እግዚአብሔር ድልን ሰጠ - ይህ ታሪክ እግዚአብሔር በእርሱ የሚታመኑትን ስለመርዳቱ ነው፡፡**

| | |
|---|---|
| | **እየተማርን ያለነው:**<br>• በእርሱ ላይ ሲደገፉ እግዚአብሔር እስራኤላውያንን ረዳ፡፡<br>• በህይወታችን ውስጥ ድል መንሳት እንድንችል እግዚአብር ወደ እርሱ እንድንጸልይ ይፈልጋል፡፡<br><br>**ቁልፍ ጥቅስ: *ዘጸአት 17፡ 15***<br>**የመጽሐፍ ቅዱስ የንባብ ክፍል: *ዘጸአት 17፡ 8 – 15*** |
| አስተዋውቁ | ብዙም ሳይቆይ እስራኤላውያን ሌላ ችግር ገጠማቸው፡፡ አማሌቃውያን የሚባሉ የጠላት የጦር ሰራዊት እነሱን ማጥቃት ጀመረ፡፡ ***(ዘጸአት 17፡ 8)***<br>*ልጆቹ ስለሁኔታው እንዲያስቡ ለማድረግ ከዚህ በታች ያሉትን ጥያቄዎች ተጠቀሙ፡፡*<br>• *እስራኤላውያን ምን ማድረግ አለባቸው? (መልሶ ማጥቃት)*<br>• *መዋጋት ለምደዋል? በግብፅ ባሪያዎች እንጂ ወታደሮች እንዳልነበሩ ልጆቹን አስታውሱ፡፡*<br>• *ምን ተሰምቷቸው ነበር?*<br>• *በእግዚአብሔር እርዳታ መተማመን ይችላሉ? እግዚአብሔር ወደ አዲስ ምድር ሊያመጣቸው ከግብፅ እንዳወጣቸው ልጆቹን አስታውሱ፡፡ የገባውን ቃል ይጠብቃል፡፡* |
| አስተምሩ | • *ሙሴ ጥበበኛ መሪ ነበር እና ምን ማድረግ እንዳለበት ያውቃል፡፡ ረዳቱን እያሱን የጦር ሰራዊት እንዲመርጥ ጠየቀው፡፡ ሰራዊቱ የእዚአብሄር እርዳታ እንደሚያስፈልገው ሙሴ ያውቅ ነበር፣ ስለሆነም ከአሮንና ከሖር ጋር የጦር ሜዳውን ከላይ ለማየት የኮረብታ አናት ላይ ወጣ፡፡ ሙሴ ሁለቱንም እጁን ተጠቅሞ በትሩን (እሱ እረኛ በነበረበት ጊዜ የሚጠቀምበትን ረዥም ዱላ) ከጭንቅላቱ በላይ አነሳ፡፡ እስራኤላውያን እንዲያሸንፉ እንዲረዳቸው በእግዚአብሔር እንደታመኑ ያሳዩበት መንገድ ነበር፡፡* ***(ዘጸአት 17፡ 9)***<br><br>• *ሙሴ ይህንን እስካደረገ ድረስ እስራኤላውያን እያሸነፉ ነበር፡፡ እጃቸውን ከጭንቅላታቸው በላይ እንዲይዙ ልጆቹን ጠይቋቸው፡፡ ለረዥም ጊዜ እንደዛ ወደላይ አድርጋችሁ ብትቆዩ እጃችሁ ምን የሚሆን ይመስላችኋል? ብዙም ሳይቆይ የሙሴ እጆች ደከሙና ለእረፍት ወደታች አወረዳቸው፡፡ ከዛም ጠላት ማሸነፍ ጀመረ፡፡ አሮን እና ሖር ሙሴን እንዴት ረድተውት ሊሆን እንደሚችል ልጆቹን ጠይቁ ከዛም ያደረጉትን በትክክል ግልፅ አድርጉ፡፡ ከዛም ሙሴ ጸሀይ እስክትጠልቅ ድረስ እጁን ማንሳት ቻለ እና በዚያ ጊዜ እስራኤላውያን አሸነፈው ነበር፡፡ ሙሴ ስለድሉ እግዚአብሔርን ማመስገን ፈለገ ስለዚህ የድንጋይ መሰዊያ ሰራና "ጌታ ሰንደቄ ነው" ብሎ ጠራው፡፡ ሙሴ እግዚአብሔር ለድሉ ክብሩን ሁሉ እንዲወስድ ፈልጎ እንደነበር አብራሩ፡፡* ***(ዘጸአት 17፡ 10 – 13፣ 15)***<br><br>• *ጦርነቱን ለማሸነፍ በጣም አስፈላጊ ድርሻ የነበረው ማን ይመስላችኋል? ሙሴ ወደ እግዚአብሔር እጁን ባያነሳና በእርሱ ባይደገፍ ኖሮ እያሱ እና ወታደሮቹ ይህንን ጦርነት አያሸንፉም ነበር፡፡ ጌታ ኢየሱስን እንደ አዳኛችን ካመንነው፣ እኛም ጠላት አለን - ሴጣን፡፡ ፈሪ ሊያደርገንና በህይወታችን ውስጥ ያለውን ደስታ ሊወስድ ይፈልጋል፡፡ ማን ነው የበለጠ ሀይለኛ ጌታ ኢየሱስ ወይስ ሴጣን? ኢየሱስ የበለጠ ሀይለኛ ስለሆነ ድል መንሳት እንችላለን፡፡ ሁልጊዜ በእርሱ መደገፍ አለብን፡፡*<br><br>**የመጽሐፍ ቅዱስ ጊዜ ትምህርቱን አጠናቁ፡፡**<br>**አሳዩ፡** FBI ሙሴ ሲጸልይ እስራኤላውያን ከአማሌቃውያን ጋር ታገሉ፡፡ |
| አስጠኑ | ቁልፍ ጥቅሱን አስፈላጊ በሆነበት ቦታ ላይ አስተምሩና አስረዱ ፡፡ ***ዘጸአት 17፡ 15*** |
| እዲታወስ | ልጆቹ ትልቅ ያጌጠ "ጌታ ሰንደቄ ነው" የሚል ሰንደቅ መስራት ይችላሉ፡፡ እንደ አማራጭ እነዚህን ጥያቄዎች በፈተና ውስጥ መጠቀም ትችላላችሁ:<br>• የእስራኤላውያን የጦር ሰራዊት መሪ ማን ነበር?<br>• ሙሴ የት ነበር የሄደው?<br>• ማን ነበር ከሙሴ ጋር የሄደው?<br>• ሙሴ ክንዱን ከፍ ሲያደርግ ጦርነቱ ውስጥ ምን ተፈጥሮ ነበር?<br>• ሙሴ ለምን ያህል ጊዜ ነበር ክንዱን ከፍ ያደረገው?<br>• ማን ነበር ድሉን የሰጠው? |

<u>**ለ11 ታሪክ 3**</u>

**እግዚአብሔር ትዕዛዛትን ሰጠ - ይህ ታሪክ ስለ እግዚአብሔር ህጎች ነው፡፡**

<table>
<tr><td></td><td>እየተማርን ያለነው፡<br>• እግዚአብሔር ቅዱስ ነው፡፡<br>• የእግዚአብሔርን ትዕዛዛት መጠበቅ አንችልም፡፡<br><br>ቁልፍ ጥቅስ፡ ዘጸአት 20፡ 1 ወይም ሮሜ 3፡ 23<br>የመጽሐፍ ቅዱስ የንባብ ክፍል፡ ዘጸአት 19 – 20</td></tr>
<tr><td>አስተዋውቁ</td><td>በትምህርት ቤት ወይም በቤት ውስጥ ስላሉ ህጎች አውሩ፡፡ ምንድን ናቸው? ለምንድን ነው ህጎች ያሉን? ህጎችን ማክበር ሁሌም ቀላል ነውን? በዛሬው ትምህርት እግዚአብሔር ለእስራኤላውያን እንዴት ህጎቹን እንደሰጠ እንማራለን፡፡</td></tr>
<tr><td>አስተምሩ</td><td>• እስራኤላውያን ሲና ተብሎ ወደሚጠራ ድንኳኖቻቸውን ወደተከሉበት ወደአንድ ትልቅ ተራራ ደረሱ፡፡ እግዚአብሔር ጥቅጥቅ ባለ ደመና ወደ ተራራው አናት እንደሚወርድ ለሙሴ ነገረው፡፡ ከህዝቡ ማካከል ማንም ለመውጣት እዳይሞክር በተራራው ግርጌ ዙሪያ ምልክት የሚሆኑ ድንጋዮች ማስቀመጥ ነበረበት፡፡ ሰዎቹ ታጥበው ራሳቸውን ቢያዘጋጁም እንኳን ሀጢያታቸው ግን ወደ እግዚአብሔር መቅረብ አይችሉም ማለት ነው፡፡ (ዘጸአት 19፡ 1 – 14)<br><br>• ከሶስት ቀን በኋላ ህዝቡ በተራራው ግርጌ ቆመ፡፡ ከተራራው ጭስ ወጣ እና ተራራው ተናወጠ፡፡ ይህ እግዚአብሔር ምን ያህል ሀያል መሆኑን ለህዝቡ እንዳሳያቸው አስረዱ፡፡ ሰዎቹ ምን ተሰምቷቸው እንደነበር አስቡ፡፡ እግዚአብሔር ሙሴን ወደላይ እንዲወጣ ጠራውና ለሁለተኛ ጊዜ ከታች እንዲቆዩ ህዝቡን እንዲያስጠነቅቅ ለሙሴ ነገረው፡፡<br>(ዘጸአት 19፡ 16 – 22) እግዚአብሔር ቅዱስ ነው (ያለምንም ኃጢአት)፣ ነገር ግን ህዝቡ በህይወታቸው ኃጢአት ስላለ እርሱን መቅረብ እንዳልቻሉ አስረዱ፡፡ ኃጢአታችን ይቅር ካልተባለ በስተቀር ዛሬም ኃጢአት ከእዚአብሄር ይለየናል፡፡<br><br>• በኋላ ሙሴ በሁለት ትላልቅ ድንጋዮች ላይ የተፃፉ አስሩን ትዕዛዛት ከእግዚአብሔር ተቀበለ፡፡ ትዕዛዛቶቹ የእግዚአብሔር ህጎች ወይም መመሪያዎች ነበሩ እና እግዚአብሔር ህዝቡ እንዴት እንዲኖሩ እንደሚፈልግ ግልፅ አድርገውት ነበር፡፡ ከማንም አብልጠው እግዚአብሔርን መውደድ እና እርስ በእርስም መዋደድ ነበረባቸው፡፡ ከደረጃ 2 ህፃናት ጋር እነዚህን ብታነቡና እያንዳንዱን በአጭሩ ብታስረዱ ተገቢ ነው፡፡ እኛ ልንፈፅማቸው እንዳልቻልን እንዲረዱ አግዟቸው!<br>(ዘጸአት 20)<br><br>• በሚያሳዝን ሁኔታ እስራኤላውያን የእግዚአብሔርን ህጎች መጠበቅ አልቻሉም ነበር እና እኛም አንችልም፡፡ ሁላችንም እግዚአብሔር ከሚጠብቀው እንጎድላለን፡፡ ሀጢያተኞች ነን፡፡ በምድር ላይ ፍፁም ህይወት የኖረው ሰው ጌታ ኢየሱስ ብቻ ነው፡፡ ለዚህ ነው አዳኛችን መሆን የቻለው፡፡ እግዚአብሔር ይቅር እንዲለን የኃጢአታችንን ቅጣት ለመውሰድ ነበር የሞተው፡፡ ከዚያም የእግዚአብሔር ቤተሰብ መሆን እንችላለን እና እንደ እስራኤላውያን ከእርሱ መራቅ የለብንም፡፡<br><br>የመጽሐፍ ቅዱስ ጊዜ ትምህርቱን አጠናቁ፡፡<br>አሳዩ፡ FBI ሙሴ በሲና ተራራ ላይ አስሩን ተዕዛዛት ሲቀበል፡፡</td></tr>
<tr><td>አስጠኑ</td><td>ቁልፍ ጥቅሱን አስፈላጊ በሆነበት ቦታ ላይ አስተምሩና አስረዱ ፡፡ ዘጸአት 20፡1 ወይም ሮሜ 3፡23</td></tr>
<tr><td>እዲታወስ</td><td>ለፈተናው በደረጃ 2 ትምህርት ላይ እንደተፃፈው ትዕዛዛቶቹ ላይ ማተኮር ትችላላችሁ፡፡ ልጆቹ እንዲያዩትና እንዲሰሙትም ከተቻለ ሰሌዳ/ሰንጠረዥ ላይ ፃፉት፡፡ ሁሉንም ካነበባችሁ በኋላ የተፃፈውን አንሱት፡፡ እያንዳንዱ ተዕዛዝ ላይ ቁልፍ ቃላትን አውጡ ለምሳሌ፡- ከእኔ በቀር ሌሎች አይሁኑልህ፡፡ __________ ለአንተ አታድርግ፡፡ የጎደለውን ቃል ያወቀ ልጅ ለቡድኑ ነጥብ ሊያዝለት ይችላል፡፡</td></tr>
</table>

<u>ለ11 ታሪክ 4</u>

**እግዚአብሔር ድነትን ሰጠ - ይህ ታሪክ እግዚአብሔር ሰዎችን ከሞት ስለሚያድንበት መንገድ ነው፡፡**

<table>
<tr><td></td><td>

**እየተማርን ያለነው:**

- ከሚገባቸው ቅጣት እንዲያመልጡ እግዚአብሔር ለእስራኤላውያን መንገድ አዘጋጀ፡፡
- እግዚአብሔር የምንድንበትን መንገድ አዘጋጅቷል፡፡

**ቁልፍ ጥቅስ: *ዮሀንስ 3፡ 14***<br>
**የመጽሐፍ ቅዱስ የንባብ ክፍል: *ዘሁልቁ 21፡ 4 – 9***

</td></tr>
<tr><td>አስተዋውቁ</td><td>

አንዳንዴ ተመሳሳይ ስህተት እንሰራለን! እራኤላውያን ከግብፅ ያመጡት ምግብ ሲያልቅ ምን እንዳደረጉ ታስታውሳላችሁ? አዎ፣ አጉረመረሙና አማረሩ! እናም በዛሬው ታሪክ በድጋሜ እያጉረምረሙ ነበር! ለምን እንደሆነ እስቲ እንመልከት፡፡<br>
<u>ወይም</u><br>
በእባብ የመነደፍን አደገኝነት፣ ወደ ሆስፒታል የመሄድን አስፈላጊነትና ጸረ-ተውሳክን ስለመውሰድ አውሩ፡፡ በዛሬው ታሪክ እግዚአብሔር በእባብ ለተነደፉ ሰዎች በጣም የተለየ መድሀኒት ነበረው፡፡

</td></tr>
<tr><td>አስተምሩ</td><td>

- በሚያሳዝን ሁኔታ እስራኤላውያን በሙሴ ላይና በእግዚአብሔር ላይ ነገሮች በግብፅ እያሉ የተሻለ እንደነበር እና እግዚአብሔር ያዘጋጀውን መና እንደጠሉ ተናገሩ፡፡ ምንኛ ከሀዲዎች ነበሩ! ***(ዘኁልቁ 21፡ 5)***

- በዚህ ጊዜ እግዚአብሔር በህዝቡ ላይ ተቆጣና ሊቀጣቸው ወሰነ፡፡ ብዙም ሳይቆይ ሰፈሩ በመርዛማ እባቦች ተወረረ፡፡ *ሰዎቹ ምን ይሆናሉ?* አዎ፣ ሰዎቹ ተነደፉና አብዛኞቹ ሞቱ፡፡ ወዲያውኑ ሰዎቹ የእነሱ ጥፋት እንደሆነ አወቁ፡፡ ወደ ሙሴ መጡና ኃጢአት እንደሰሩና እባቦቹን እንዲያስወግድ ወደ እግዚአብሔር እንዲጸልይ ጠየቁት፡፡ ***(ዘኁልቁ 21፡ 6 – 7)*** *ልጆቹ፣ ስህተት ስንሰራ ይህ ትክክለኛው አኳኋን እንደሆነ እንዲያስተውሉ እርዷቸው፡፡ ኃጢአታችንን መናዘዝ እና እግዚአብሔር እንዲረዳን መጠየቅ አለብን፡፡*

- ሙሴ ወደ እግዚአብሔር ከጸለየ በኋላ፣ እግዚአብሔር ለሙሴ አንድ አዲስ ነገር እንዲያደርግ ነገረው፡፡ ከነሀስ እባብ መስራት እና በሰፈሩ ባለው ምሰሶ ላይ ከፍ አድርጎ መስቀል ነበረበት፡፡ አንጸባራቂው የነሀስ እባብ በሁሉም ሰው እይታ ውስጥ ነበር፡፡ የተነደፈ ማንኛውም ሰው የተሰቀለውን እባብ ካየ እንደማይሞት እግዚአብሔር ቃል ገባ፡፡ ይህንን ያመነና እግዚአብሔር እንዳለው ያደረገ ሁሉ በህይወት ኖረ፡፡ ሞትን ለማምለጥ ምን አይነት ቀላል መንገድ ነው! ***(ዘኁልቁ 21፡ 8 – 9)*** *(በመግቢያው ላይ ሁለተኛውን ሀሳብ ከተጠቀማችሁ፣ ማነፃጸር ትችላላችሁ) እስራኤላውያን የእግዚአብሔርን ትዕዛዝ የፈጸሙ ይመስላችኋል? ለምን? ይህ ሊኖሩ የሚችሉበት ብቸኛው መንገድ እንደነበር አፅንኦት ስጡ - ሌላ ማንኛውንም ነገር መሞከር ምንም ጥቅም አልነበረውም!*

- ከአመታት በኋላ፣ ኢየሱስ በምድር ላይ እያለ ጠቃሚ የሆነ ትምህርት ሁሉንም ለማስተማር ይህን ታሪክ ተጠቅሟል፡፡ እኛ እንደ እስስራኤላውያን ነን ምክንያቱም በእግዚአብሔር ላይ ኃጢአትን ሰርተናል እናም ኃጢአት ይቀጣል፡፡ ነገር ግን እግዚአብሔር ከኃጢአታችን ቅጣት እንድናመልጥ መንገድ አዘጋጅቶልናል፡፡ ኢየሱስ ለኃጢአታችን ሲሞት እርሱም "ከፍ ከፍ" እንደሚደረግ አብራርቷል፡፡ ኢየሱስ ባደረገልን ነገር ላይ ስንታመን፣ እግዚአብሔር ያድነንና የዘላለም ህይወት ይሰጠናል፡፡ *መዳን የምንችለው በኢየሱስ በኩል ብቻ እንደሆነ አፅንኦት ስጡ እና ምላሽ ስለመስጠታቸው አስፈላጊነት ልጆቹን አነሳሱ፡፡*

**የመጽሐፍ ቅዱስ ጊዜ ትምህርቱን አጠናቁ፡፡**<br>
**አሳዩ፡** FBI **ሙሴ** እና የነሀሱ እባብ፡፡

</td></tr>
<tr><td>አስጡኑ</td><td>

ቁልፍ ጥቅሱን አስፈላጊ በሆነበት ቦታ ላይ አስተምሩና አስረዱ ፡፡ ***ዮሀንስ 3፡ 14*** እነዚህ የኢየሱስ ቃላት እንደሆኑ ጥቀሱ፡፡ በመስቀል ላይ ከፍ ሲደረግ እንዴት ሊያድነን እንደሚችል አስረዳ፡፡

</td></tr>
<tr><td>እንዲታወስ</td><td>

አንድ ትንሽ የልጆች ቡድን የነሀሱን እባብ በእንጨት ላይ ሆኖ የሚያሳይ ስዕል እና ሌላ ቡድን ደግሞ የመስቀሉን ስዕል መስራት ይችላሉ፡፡ ያለቀው የስዕል ስራ ላይ ጥቅሱን ማሳየት ይቻላል፡፡<br>
<u>ወይም</u> በለ11 ውስጥ ያሉ ታሪኮች ላይ ሁሉ በመመስረት ፈተና ልትሰጡ ትችላላችሁ፡፡

በለ11 ላይ ተጨማሪ ጥያቄዎች የሚከተሉትን ሊያካትቱ ይችላሉ፡

- አሁን እስራኤላውያን ስለምን ነበር ያጉረመረሙት?
- እግዚአብሔር እንዴት ነበር የቀጣቸው?
- ከእባብ ንክሻ ለመዳን ህዝቡ ምን ማድረግ ነበረበት?
- ከኃጢአታችን ቅጣት እንዴት ነው መዳን የምንችለው?

</td></tr>
</table>

## <u>ለ12 ታሪክ 1</u>

**ዮሴፍ እና መልአኩ - ይህ ታሪክ ዮሴፍ ከባድ በሆነበት ጊዜ እንኳን ለእግዚአብሔር ስለመታዘዙ ነው፡፡**

**እየተማርን ያለነው፡**

- ‘ኢየሱስ’ የሚለው ስም ‘አዳኝ’ ማለት ነው፡፡
- እንደ ዮሴፍ ሁሌም እግዚአብሔርን መስማት እና መታዘዝ አለብን፡፡

**ቁልፍ ጥቅስ፡** ***ማቴዎስ 1፡ 21***
**የመጽሐፍ ቅዱስ የንባብ ክፍል፡** ***ማቴዎስ 1፡ 18-25***

### አስተዋውቁ

ስለስሞች አውሩ - ስማቸው ምን ማለት እንደሆነ ወይም ስማቸው ለምን እንደተሰጣቸው የሚያውቁ ከሆነ ልጆቹን ጠይቁ፡፡

ዛሬ ልጆቹ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በጣም ልዩ የሆነ ስም ስለተሰጠው በጣም ልዩ የሆነ ህፃን እንደሚማሩ አስረዱ፡፡ ታሪኩ ስለማን ሊሆን እንደሚችል እንዲገምቱ ለልጆቹ እድል ስጡ፡፡

### አስተምሩ

- ዮሴፍ እና ማርያም ለመጋባት እያቀዱ ነበር፣ ነገር ግን አንድ ቀን ማርያም ለዮሴፍ ልጅ ልትወልድ እንደሆነ ነገረችው፡፡ ዮሴፍ የልጁ አባት እንዳልሆነ ያውቅ ነበር ስለዚህ ማርያምን ላለማግባት ወሰነ፡፡ (***ማቴዎስ 1፡ 18-19***)
- አንድ ቀን ሌሊት ዮሴፍ ህልም አለመ፡፡ በህልሙ አንድ መልአክ ታየውና ዮሴፍን አናገረው፡፡ መልአኩ "ማርያምን እንደሚስትህ ለመውሰድ አትፍራ ምክንያቱም ልጁ የተጸነሰው ከመንፈስ ቅዱስ ነውና፡፡" አለው፡፡ (***ማቴዎስ 1፡ 20***) *ይህ ማለት ልጁ የእግዚአብር ልጅ ይሆናል ማለት እንደሆነ ለልጆቹ አስረዱ፡፡*
- ሰዎችን ከሀጢያታቸው ያድናቸዋልና መልአኩ ህፃኑን ‘ኢየሱስ’ ብሎ እንዲጠራው ለዮሴፍ ነገረው፡፡ (***ማቴዎስ 1፡ 21***) *ኢየሱስ "አዳኝ" ማለት እደሆነ አስረዱ፣ አዳኝ ምን እንደሆነ አብራሩ (በዕለት ተዕለት ህይወት ለምሳሌ፡- የመስመጥ አደጋ ውስጥ ያለ ሰው የሚያድነው ወይም የሚያወጣው ያስፈልገዋል፡፡ አዳኝ ለምን እንደሚያስፈልገን ልጆቹን ጠይቁ (ኃጢአት ስላደረግን ነው)፡፡ ኢየሱስ አዳኛችን ለመሆን እንዴት እንደቻለ ምን እንዳደረገ ልጆቹን ጠይቁ፡፡ (ለእኛ ብሎ ከሰማይ ወርዶ በመስቀል ላይ ሞተ)*
- ዮሴፍ ከህልሙ ሲነቃ እንደተባለው አደረገና ማርያምን አገባ፡፡ ከተወሰነ ጊዜ በኋላ ህፃኑ ተወለደና፣ ዮሴፍ ‘ኢየሱስ’ አለው፡፡ (***ማቴዎስ 1፡ 24-25***) *ዮሴፍ ስለተሰጠው መመሪያ ልጆቹን ጠይቁና እንዴት እንደተገበረው አብራሩ፡፡ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ያለውን የእግዚአብርን መመሪያ መስማታችንና ማድረጋችን ምን ያህል አስፈላጊ እንደሆነ አስረዱ፡፡ አንድ ላይ በመሆን፣ እግዚአብሔር እንድንከተላቸው የሰጠንን አንዳንድ መመሪያዎች አስቡና ዝርዝር አዘጋጁ፡፡*

**የመጽሐፍ ቅዱስ ጊዜ ትምህርቱን አጠናቁ፡፡**
**አሳዩ፡** FBI መልአክ ዮሴፍን ጎበኘ፡፡

### አስጠኑ

ቁልፍ ጥቅሱን አስፈላጊ በሆነበት ቦታ ላይ አስተምሩና አስረዱ፡፡ ***ማቴዎስ 1፡ 21***

### እዲታወስ

ታሪኩን ለመከለስ እንዲረዳ ልጆቹን ቀጥሎ ያሉትን ጥያቄዎች ጠይቋቸው፡፡

- ዮሴፍ ማንን ነበር ሊያገባ የነበረው?
- ማርያም ለዮሴፍ ምን ዜና ነበር የነገረችው?
- እግዚአብሔር ዮሴፍን እንዴት ነበር ያናገረው?
- የልጁ አባት ማን ነበር?
- ልጁ ማን ተብሎ ሊጠራ ነበር?
- ‘ኢየሱስ’ የሚለው ስም ምን ማለት ነው?
- ከህልሙ ከነቃ በኋላ ዮሴፍ ምን ነበር ያደረገው?
- እንድንከተለው እግዚአብሔር የሰጠንን አንድ መመሪያ አስቡ፡፡

## ለ12 ታሪክ 2

**ሄሮድስ እና ሰብአ ሰገሎች - ይህ ታሪክ ኢየሱስን ለማግኘት ስለሞከሩ ሰብአ ሰገሎች ነው፡፡**

<table>
<tr><td></td><td>እየተማርን ያለነው፡<ul><li>ኢየሱስ የነገስታት ንጉስ ነው፡፡</li><li>ኢየሱስ ሊመለክ ይገባዋል፡፡</li></ul>ቁልፍ ጥቅስ፡ ማቴዎስ 2፡ 2<br>የመጽሐፍ ቅዱስ የንባብ ክፍል፡ ማቴዎስ 2፡ 1-8</td></tr>
<tr><td>አስተዋውቁ</td><td>ልጆቹ አስፈላ ስለሆኑ ሰዎች እንዲያስቡ ጠይቋቸው፡፡ የእነሱን ዝርዝር አዘጋጁ፡፡<br>ተወያዩ - ከእነዚህ ሰዎች መካከል ማግኘት የምትፈልጉት አለ? ምን ታደርጋላችሁ? እንዴት ነው የምታደርጓቸው?<br>ዛሬ በምድር ላይ ከኖሩት ሰዎች ሁሉ እጅግ በጣም አስፈላጊ የሆነውን ሰው ለማግኘት ጉዞ ስለተጓዙ ስለሆኑ ሰዎች እንማራለን፡፡</td></tr>
<tr><td>አስተምሩ</td><td><ul><li>አዲስ ኮከብ ሰማዩ ላይ ታየ፡፡ በምስራቅ የሚኖሩ ሰብአ ሰገሎች ይህ የአዲስ ንጉስ መወለድ ምልክት እንደሆነ ያውቁ ነበር፡፡ አዲሱን ንጉስ ለመፈለግ ወደ እየሩሳሌም ተጓዙ፡፡ ወደ ንጉስ ሄሮድስ ሄደው "የአይሁድ ንጉስ ሆኖ የተወለደው የት አለ? ሰማይ ላይ ሲወጣ ኮከቡን አይተነዋል እና ልናመልከው መጥተናል" አሉት፡፡ (ማቴዎስ 2፡ 1-2) ሊወለድ የነበረው አዲሱ ንጉስ ኢየሱስ ነበር፣ የእግዚአብሔር ልጅ እና በምድር ላይ ከኖረ ከማንኛውም ንጉስ እንደሚበልጥ ለልጆቹ አስረዱ፡፡ ኢየሱስ የነገስታት ንጉስ ነው፡፡ ከቀደመው ትምህርት የኢየሱስ ስም ምን ማለት እንደሆነ ማስታወስ ከቻሉ ልጆቹን ጠይቁ፡፡ ሰብአ ሰገሎች ንጉሱን 'ማምለክ' እንፈልጋለን ሲሉ ምን ለማለት ፈልገው እንደሆነ አብራሩ፡፡ ኢየሱስ ለምንድነው ሊመለክ የሚገባው?</li><li>ሄሮድስ ስለአዲስ ንጉስ ሲሰማ ተጨንቆ ነበር፡፡ ሌላ ማንም ቦታውን እንደንጉስ እንዲወስድ አልፈለገም ነበር፡፡ አንዳንድ አማካሪዎቹን ጠርቶ አዲሱ ንጉስ የት እንደሚወለድ ጠየቃቸው፡፡ ቅዱሳን መፃህፍትን ከመረመሩ በኋላ ቤቴልሄም በሚባል ከተማ ውስጥ እንደሚወለድ አወቁ፡፡ (ማቴዎስ 2፡ 3-6)</li><li>ሄሮድስ ሰብአ ሰገሎችን ጠርቶ "ሂዱና ልጁን አግኙት፣ ስታገኙት እኔም ሄጄ እንዳመልከው ተመልሳችሁ መታችሁ የት እንዳለ ንገሩኝ" አላቸው፡፡ (ማቴዎስ 2፡ 7-8) ሄሮድስ አዲሱን ንጉስ ሊያመልክ እንዳልፈለገና ሊገድለው እንደፈለገ አስረዱ፡፡ ሄሮድስ አዲሱን ንጉስ ሊገድለው እንደሚፈልግ ለምን እንዳሰቡ ልጆቹን ጠይቁ፡፡ በዚህም ጊዜ ብዙ ሰዎች ለኢየሱስ መሆን እንዳለባቸው አይሆኑም ነገር ግን እግዚአብሔር ልክ ሰብአ ሰገሎች እንዳደረጉት ኢየሱስን እንድንወደውና እንድናመልከው እንደሚፈልግ አስረዱ፡፡</li></ul>የመጽሐፍ ቅዱስ ጊዜ ትምህርቱን አጠናቁ፡፡<br>አሳዩ፡ FBI ሰብአ ሰገሎች ለኢየሱስ ሰገዱ፡፡</td></tr>
<tr><td>አስጠኑ</td><td>ቁልፍ ጥቅሱን አስፈላጊ በሆነበት ቦታ ላይ አስተምሩና አስረዱ፡፡ ማቴዎስ 2፡ 2</td></tr>
<tr><td>እዲታወስ</td><td>ታሪኩን ለመከለስ እንዲረዳ ልጆቹን ቀጥሎ ያሉትን ጥያቄዎች ጠይቋቸው፡፡<ul><li>ሰማዩ ላይ ምን ታየ?</li><li>ሰብአ ሰገሎች ከየት አቅጣጫ ነበር የመጡት?</li><li>አዲሱን ንጉስ ለማየት የት ነበር የሄዱት?</li><li>ያናገሩት ንጉስ ስም ማን ነበር?</li><li>ስለአዲስ ንጉስ ሲሰማ ንጉስ ሄሮድስ ምን ነበር የተሰማው?</li><li>ንጉሱ በየትኛው ከተማ እንደሚወለድ ነበር ያወቁት?</li><li>ሄሮድስ ሰብአ ሰገሎች ምን እንዲያደርጉ ነበር የነገራቸው?</li><li>ከማንኛውም ሌላ ንጉስ የሚበልጠው ማነው?</li></ul></td></tr>
</table>

## ለ12 ታሪክ 3

**ኢየሱስ እና ሰብአ ሰገሎች - ይህ ታሪክ ሰብአ ሰገሎች ኮከቡን ስለመከተላቸውና ኢየሱስን ስለማግኘታቸው ነው፡፡**

<table>
<tr><td></td><td>እየተማርን ያለነው፡<br>• እስከ ዛሬ ከተወለዱት ህፃናት ሁሉ በጣም የላቀ ስለሆነ ሰብአ ሰገሎች ለኢየሱስ ሰገዱና በጣም ልዩ የሆኑ ስጦታዎችን ሰጡት፡፡<br>• አሁንም ላደረገው ነገር ሁሉ በማመስገንና የሚያስደስተውን ነገሮች በማድረግ ኢየሱስን ማምለክ እንችላለን፡፡<br><br>ቁልፍ ጥቅስ፡ ማቴዎስ 2፡ 11<br>የመጽሐፍ ቅዱስ የንባብ ክፍል፡ ማቴዎስ 2፡ 9-12</td></tr>
<tr><td>አስተዋውቁ</td><td>ተወያዩ - ተሰጥቷችሁ ከሚያውቅ ስጦታ ሁሉ በጣም አስደናቂው ስጦታ ምንድነው? (ልጆቹ የስጦታውን ሰዕል እንዲስሉ ማድረግ ትችላላችሁ)፡፡<br>አዲስ ህፃን ልትጠይቁ ቢሆን ምን ስጦታ ልትወስዱላቸው ትችላላችሁ?<br><br>ዛሬ ሰብአ ሰገሎች ስለሰጡት ስጦታዎች እንደምንማር ለልጆቹ አስረዱ፡፡<br>ባለፈው ትምህርት ላይ ስለ ሰብአ ሰገሎች የተማሩትን ደግመው እንዲነግሯችሁ ልጆቹን ጠይቁ፡፡</td></tr>
<tr><td>አስተምሩ</td><td>• ሰብአ ሰገሎች ሄሮድስን ትተው መንገዳቸውን ሄዱ፡፡ ኮከቡን በድጋሚ አዩና ኢየሱስ ወዳለበት ቦታ መራቸው፡፡ ሰብአ ሰገሎች ኮከቡን ሲያዩ በጣም ተደስተውና ጓጉተው ነበር፡፡ (ማቴዎስ 2፡ 9-10) ተወያዩ - ኮከቡን ሲያዩ ሰብአ ሰገሎች በጣም የጓጉት ለምን ይመስላችኋል?<br>• ሰብአ ሰገሎች በቤተልሄም ውስጥ ዮሴፍ፣ ማርያምና ህፃኑ ኢየሱስ ወዳሉበት ቤት ደረሱ፡፡ ወደ ውስጥ ገቡና ህፃኑን ኢየሱስ ሲያዩት ወድቀው ሰገዱለት፡፡ ሶስት ስጦታዎችን ሰጡት፡ ወርቅ፣ እጣንና ከርቤ፡፡ (ማቴዎስ 2፡ 11) እነዚህ ስጦታዎች ለህፃን ሊሰጡ ከሚያስቡት ስጦታ ጋር ተመሳሳይ ከሆነ ልጆቹን ጠይቁ፡፡ እነዚህ ስጦታዎች በጣም ውድና አብዛኛውን ጊዜ የሚሰጡት ለንጉስ ብቻ እንደነበር አስረዱ፡፡ ተወያዩ - ለምን ይመስላችኋል ሰብአ ሰገሎች እነዚህን ስጦታዎች ለህፃኑ ኢየሱስ ለመስጠት የፈለጉት? እንደ ሰብአ ሰገሎች ስጦታ መስጠት ባንችልም እንኳን ስላደረገው ነገር ሁሉ በማመስገን እና የሚያስደስተውን ነገር በማድረግ እግዚአብሔርን ማምለክ እንደምንችል አስረዱ፡፡<br>• ከተወሰነ ጊዜ በኋላ ሰብአ ሰገሎች ወደ ቤታቸው የሚመለሱበት ጊዜ ነበር፡፡ ሄሮድስ ተመልሰው እንዲመጡና ህፃኑን የት እንዳገኙት እንዲነግሩት ጠይቋቸው ነበር፣ ነገር ግን ወደ ሄሮድስ እንዳይመለሱ እግዚአብሔር በህልም አስጠነቀቃቸው ስለዚህ በሌላ መንገድ ወደ ቤታቸው ሄዱ፡፡ (ማቴዎስ 2፡12) ተወያዩ - ሰብአ ሰገሎች ወደ ቤታቸው ሲሄዱ ሳለ ምን የተሰማቸው ይመስላችኋል? ቤት ሲደርሱ ለሰዎች ምን የተናገሩ ይመስላችኋል?<br><br>የመጽሐፍ ቅዱስ ጊዜ ትምህርቱን አጠናቁ፡፡<br>አሳዩ፡ FBI ሰብአ ሰገሎች ለኢየሱስ ሰገዱ፡፡</td></tr>
<tr><td>አስጠኑ</td><td>ቁልፍ ጥቅሱን አስፈላጊ በሆነበት ቦታ ላይ አስተምሩና አስረዱ፡፡ ማቴዎስ 2፡ 11</td></tr>
<tr><td>እዲታወስ</td><td>ታሪኩን ለመከለስ እንዲረዳ ልጆቹን ቀጥሎ ያሉትን ጥያቄዎች ጠይቋቸው፡፡<br>• ሰብአ ሰገሎች ሰማዩ ላይ በድጋሚ ምን አዩ?<br>• ኮከቡን ሲያዩ ምን ነበር የተሰማቸው?<br>• ኮከቡ ወዴት ነበር የመራቸው?<br>• ቤቱ ውስጥ ማን ነበር?<br>• ሰብአ ሰገሎች ኢየሱስን ሲያዩ ምን አደረጉ?<br>• ስንት ስጦታዎች ነበር የሰጡት?<br>• የአንዱን ሰጦታ ስም ጥቀሱ፡፡<br>• ሰብአ ሰገሎች በሌላ መንገድ ወደ ቤት መሄድ እንዳለባቸው ያወቁት እንዴት ነበር?</td></tr>
</table>

## ለ12 ታሪክ 4
**ወደ ግብጽ ሽሽት - ይህ ታሪክ እግዚአብሔር ልጁን ስለመንከባከቡ ነው፡፡**

| | |
|---|---|
| | **እየተማርን ያለነው:**<br>• እግዚአብሔር ልጁን ኢየሱስን ጠብቆታል፡፡<br>• ኢየሱስ፣ ማርያም እና ዮሴፍ እንዳረጉት እግዚአብሔርን ማስደሰት አለብን፡፡<br><br>**ቁልፍ ጥቅስ:** ***ማቴዎስ 2፡ 15***<br>**የመጽሐፍ ቅዱስ የንባብ ክፍል:** ***ማቴዎስ 2፡ 13-23*** |
| አስተዋውቁ | አይተውት ስለሚያውቁት ስለማንኛውም ህልም እንዲነግሯችሁ ልጆቹን ጠይቋቸው፡፡<br>በመጽሐፍ ቅዱስ ዘመን ህልሞች ብዙ ጊዜ ልዩ ትርጉሞች እንደነበራቸው ልጆቹን አስታውሱ፡፡ እስካሁን ድረስ በታሪክ ውስጥ ስለተማሯቸው ህልሞች እንዲነግሯችሁ ጠይቋቸው (የዮሴፍ ህልም፣ የሰብአ ሰገሎች ህልም)፡፡<br>ዛሬ ስለ ሌላ ህልም ነው የምንማረው፡፡ |
| አስተምሩ | • ሰብአ ሰገሎች ከሄዱ በኋላ ዮሴፍ ሌላ ህልም አለመ፡፡ በህልሙ እግዚአብሔር፣ ሄሮድስ በጣም እንደተናደደና ኢየሱስን ሊገድል እንደሚሞክር ለዮሴፍ ነገረው፡፡ እግዚአብሔር ደህና እንዲሆኑ ኢየሱስና ማርያምን ይዞ ወደ ግብፅ መሸሽ እንዳለበት ለዮሴፍ ነገረው፡፡ (***ማቴዎስ 2፡ 13***) *ተወያዩ - ዮሴፍ ይህንን ህልም ሲያይ ምን የተሰማው ይመስላችኋል?*<br>• በድጋሚ ዮሴፍ የተባለውን አደረገና ቤተሰቡን ወደ ግብፅ ወሰደ፡፡ ንጉስ ሄሮድስ መሞቱን እስኪሰሙ ድረስ ለተወሰነ ጊዜ እዚያው ቆዩ፡፡ (***ማቴዎስ 2፡ 14-15***) *ተወያዩ - ዮሴፍ እግዚአብሔር በህልሙ እንደነገረው ባያደርግ ኖሮ ምን የሚፈጠር ይመስላችኋል? ዮሴፍ እግዚአብሔር እንደነገረው ማድረጉ በጣም አስፈላጊ ነበር፡፡ መጽሐፍ ቅዱስ ኢየሱስ ከመወለዱ ከብዙ መቶ አመታት በፊት ስለመወለዱ አስቀድሞ እንደተናገረ ለልጆቹ ተናገሩ፡፡ ቢቃል የሚያዘው ጥቅስ ኢየሱስ በግብፅ ውስጥ ስለመሆኑ እንደሚናገር አስረዱ - ከመሆኑ ከብዙ ጊዜ በፊት ሄሮድስ ምን ለማድረግ እንደሚሞክር እግዚአብሔር ያውቅ ነበር፡፡ በተፈጠረው ነገር ሁሉ ውስጥ እግዚአብሔር ልጁን እየጠበቀ ነበር፡፡*<br>• ሄሮድስ ሲሞት ዮሴፍ፣ ማርያምና ኢየሱስ ተመለሱና ናዝሬት ወደሚባል ከተማ ለመኖር ሄዱ፡፡ (***ማቴዎስ 2፡ 19-23***) *ኢየሱስ በናዝሬት በሚያድግበት ጊዜ ቤተሰቡን፣ ጎረቤቶቹንና ከሁሉም በላይ ደግሞ አባቱን እግዚአብሔርን ሁሌም ያስደስት እንደነበር ለልጆቹ ተናገሩ፡፡ እግዚአብሔር እርሱንም የሚያስደስተውን ነገር እንድናደርግ እንደሚፈልግ ልጆቹን አስታውሷቸው፡፡ እርሱን ለማስደሰት የምናደርገው ምርጡ ነገር አዳኛችን እንዲሆን ኢየሱስን ስለላከው ማመስገንና ለኃጢአታችን ይቅርታን በመጠየቅ ነው፡፡*<br><br>**የመጽሐፍ ቅዱስ ጊዜ ትምህርቱን አጠናቁ፡፡**<br>**አሳዩ:** FBI መልአክ ዮሴፍን ጎበኘ፡፡ |
| አስጠኑ | ቁልፍ ጥቅሱን አስፈላጊ በሆነበት ቦታ ላይ አስተምሩና አስረዱ፡፡ ***ማቴዎስ 2፡ 15*** |
| እዲታወስ | ታሪኩን ለመከለስ እንዲረዳ ልጆቹን ቀጥሎ ያሉትን ጥያቄዎች ጠይቋቸው፡፡<br>• ሰብአ ሰገሎች ከሄዱ በኋላ ዮሴፍ ምን ሆነ?<br>• ዮሴፍ የት እንዲሄድ ነበር እግዚአብሔር የነገረው?<br>• ለምንድነው እዛ መሄድ የነበረበት?<br>• ዮሴፍ ወደግብፅ አብሮት ማንን ነበር የወሰደው?<br>• ወደቤት መቼ ተመለሱ?<br>• ለመኖር የት ከተማ ነበር የሄዱት?<br>• በናዝሬት በሚያድግበት ጊዜ ኢየሱስ ምን አይነት ሰው ነበር?<br>• እግዚአብሔርን ለማስደሰት ምን ማድረግ እችላለን? |

## የውጤት አሞላል ለአስተማሪው መመሪያ

### ደረጃ 3 ትምህርት:

- በዚህ ጥናት ጥያቄዎቹን ለመመለስ የግድ መጽሐፍ ቅዱስንን ማንበብ ይጠበቅባቸዋል።
- ጥያቄዎቹ በተለያየ ይዘት ቀርበዋል የሰንጠረዥ ጨዋታ፣ ቃላት መፈልግና ዳሽ ሙላ፡፡
- መመለስ ያለባቸው አዲሱ መደበኛ ትረርጉምንና መደበኛውን ትርጉም መጽሐፍ ቅዱስ በመጠቀም ነው፡፡
- ጥያቄዎቹ በተቻለ አቅም የትኛውንም ትርጉም መጽሐፍ ቅዱስ ተጠቅመው እንዲመልሱ ተደርገው ነው የቀረቡት፡፡
- ለሣምንቱ ትምህርት 20 ነጥብ የተመደበ ሲሆን ይህም በወሩ ውስጥ 80 ነጥብ ይሆናል።
- ደረጃ 3 በአብዛኛው እንደተገለጸው ለአንድ ጥያቄ አንድ ነጥብ ነው የሚሰጠው።

### ደረጃ 4 ትምህርት:

- ይሄኛው ከደረጃ 3 ጠንከር ያለ ጥናት ነው፡፡
- የተወሳሰቡ ጥያቄዎችን መልስ ይፈልጋለል፡፡
- ትምህርቱ በሙሉ ሲጠናቀቅና ጥያቄዎቹ ሙሉ መልስ ስመለሱ ለሣምንቱ ሃያ ነጥቦች ለወሩ ደግሞ 80 ነጥቦች ይያዛሉ።

### የመጽሐፍ ቅዱስ ጊዜ ውጤት አያያዝ

የውጤት አያያዝ ፍንጮች
በመጀመሪያ ተማሪዎቹ:

- እያንዳንዱን ትምህርት መርምረህ በማረም ትክክለኛ ለሆኑትና ላልሆኑት ምልክት አድረግ።
- በመመሪያው መሠረት አስፈላጊ ነጥቦችን ለማበረታቻ ሸልም።
- እያንዳንዱን ትክክለኛ መልስ የሚታረመው ሁል ጊዜ በተለየ ቀለም መሆን አለበት።
- ትክክለኛውን መልስ ምንም ነጥብ ባያስቆረጥም አስፈላጊ ሲሆን የቃላት ግድፈትን አርም።
- በከፊል ለተሠሩ መልሶች ነጥብ መቀነስ ያስፈልጋል።
- የወሩን አጠቃላይ መደመርና በገፁ መጨረሻ ባለው ቦታ ሙላ። ተማሪዎቹን ለማበረታታት በመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ወቅት ሁሉን ነገር መስራትና ደግ መሆን ያስፈልጋል። አስተማሪው በየወሩ ለተማሪዎቹ የቃል ማበረታቻ በትምህርቱ መጨረሻ በተሠጠው ባዶ ቦታ ላይ መሙላት ይጠቅማል። አስተያየቶች የሚሠጡት በጥሩ አቀባብ፣ ለጥራት፣ ለውጤት፣ ትምህርትን በመረዳት ደረጃ፣ ወዘተ ሊሆኑ ይችላሉ። አስተያየቶችን በተቻለ መጠን እንዲለያዩ እንሞክር።

ጥያቄዎች፣ ዐረፍተ ነገሮች፣ ግንዛቤዎች፣ ማበረታቻዎች፣ ወዘተ የሚደጋገሙ ከሆነ የተለያየ አይነት ጥያቄን ለመጠቀም ያገለግላሉ። ማሠላሠል ቢጠይቅም የተማሪዎቹን ፍላጎት ንቁ ማድረግ ያስፈልጋል። በየወሩ ተመሣሣይ ዓረፍተ ነገር ወይም ጥያቄ የሚደጋገም ከሆነ ትኩረት አይስብም።

#### ደረጃ 3

**ጠቅላላ አስተያየቶች**: ,

ድንቅ ስራ ነው ጥያቄዎቹን በርግጥ በሚገባ አንብበሃቸዋል፡፡ በተላይ የመጨረሻውን መልስህን እጅግ ወድጄዋለሁ በተመረጡ ቃላት ነው የጻፍከው፡፡ 'ዮናታን ስለ ታታሪነትህ አመሰግንሃለሁ፡፡ ሁሉንም ጥያቄዎች ለመመለስ ጥረት አድርገሃለህ የረሳህውንም አንዱን ጽፌልሃለሁ፡፡'

**መንፈሣዊ አስተያየቶች:**

'ሙሴ ከእስራኤል ልጆች አስቸጋሪ ሁኔታ ቢገጥመውም እግዚአብሔር ከጎኑ ሆኖ አበርትቶታል' 'ዮሴፍ ከቤቱ ሩቅ በሆነ ሰዓት አባቱ እግዚአብሔርን እንዲወድ ያስተማረውን ትምህርት አልረሳም ነበር፡፡' 'በርጠሚዎስ ወደ ጌታ ኢየሱስ ለመድረስ ቆርጦ ነበር፣ ኢየሱስ የተለየ እንደነበር ለመረዳት አለማየቱ ምንም ተጽዕኖ አላሳደረበትም፡፡'

#### ደረጃ 4

**ጠቅላላ አስተያየቶች:**

ሌላ አስደናቂ ውጤት! እንደተረዳሁት ጥሩ የመጽሐፍ ቅዱስ መረዳት አለሽ ደግሞም በጥናትሽ እንደተደሰትሽ አስባለሁ፡፡ አንዳንዱ በፍጥነት የሚታለፍ ቢሆንም እንኳ ጊዜ ወስደሽ በጥንቃቄ ስለሰራሽው አመሰግናለሁ፡፡ ጥረትሽን አደንቃለሁ፡፡ በጣም ጥሩ ሞክረሻል ራሄል ከመልስሽ እንደተረዳሁት የታሪኩን ሃሳብ በደንብ አልተረዳሽውም ደግመሽ እንደምታነቢው ተስፋ አደርጋለሁ፡፡

**መንፈሣዊ አስተያየቶች:**

ምሳሌዎች አንዳንድ ጊዜ ሰማያዊ ትርጉም የያዙ ምድራዊ ታሪኮች ወይም ከዛ የጠለቁ ይሆናሉ፡፡ በጥናት 3 ስላለው ምሳሌ የጠለቀ ትርጉም ምን ማሰብ ትችላህ?
እስጢፋኖስ እጅግ አሰቃቂ ሞት ነው የሞተው እንዲያ ሆኖ ለመሞት አልፈራም ነበር ምክንያቱም እግዚአብሔር አሁንም ሁሉን እንደሚቆጣጠርና ቢሞትም ከጌታ ከኢየሱስ ጋር እንደሚሆን ያመን ስለነበር ነው፡፡

© Bible Educational Services 2015

www.besweb.com

በሕግ የተመዘገበ የዩ.ኬ ለጋሽ ድርጅት 1186004

03/2025
AM-Amharic